# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር

## *የሚኒስቴር መ/ቤቱና የተጠሪ ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት*
## *የስድስት ወራት አፈጻጸም ሪፖርት*

**ጥር 2014 ›.M.**
**አዲስ አበባ**

I.መግቢያ 3

II. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የ2014 በጀት አመት የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት 5

1. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በአዲሱ አወቃቀር መሰረት በአራት ፕሮግራሞች የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም 5

1.1 ፕሮግራም አንድ፡ ሥራ አመራርና አስተዳደር፣ 5

1.2 ፕሮግራም ሁለት የውሃ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ 6

1.3 ንኡስ ፕሮግራም ሶስት፡ የውሃና ኢነርጂ ዘርፍ ምርምርና ስርፀት 10

1.4 ፕሮግራም ሶስት፡ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ዘርፍ 21

1.4.1 በድርቅ የሚጠቁ አከባቢዎች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት 21

1.4.2 በመንግስት በጀት የሚደገፉ ፕሮጀክቶች 21

1.4.3 በCWA-II (Consolodated WaSH Account-II) በጀት የሚደገፉ ፕሮጀክቶች 23

1.4.4 የመጠጥ ውሃ ማስተባበር ፕሮጀክት 24

1.5. ፕሮግራም አራት፡ የኢነርጂ ልማትና አስተዳደር 44

1.5.1 የሃይድሮፓወር ጥናትና ዲዛይን ንኡስ ፕሮግራም 44

1.5.2 ንኡስ ፕሮግራም አምስት፡ ብሔራዊ ኤሌክትሪፊኬሽን 48

II. የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት 49

*2.1 የኢ.ት/ያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትቲዩት 49*

***2.2 የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት 53***

**III. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች 58**

**IV. ማጠቃለያ 60**

## I.መግቢያ

የዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ውሃን ማእከል ባደረገው፡ የውሃና ኢነርጂው ክፍለ ኢኮኖሚ የአገራችንን ልማት በወሣኝ መልኩ ለማሳደግ ትኩረት ከተሰጣቸው የኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና አካባቢያዊ መሰረተ ልማት ዘርፎች አንዱ ሲሆን ይህን ታላቅ ኃላፊነት ለመወጣትና በሴክተሩ የአምስት አመት የዕቅድ ዘመን ተግባራዊ ለማድረግ የተያዙ ግቦችን ለማሳካት በስሩ በተዋቀሩ ፕሮግራሞችና ተጠሪ ተkማት አማካኝነት የተለያዩ የልማት ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ከአዲሱ የሪፎርም ሥራ በኃላ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሥሩ በሦሥት ዋና ዋና ዘርፎችና በሦሥት ተጠሪ ተቋማት ተደራጅቷል፡፡ዘርፎቹም የመጠጥ ዉሃና ሳኒቴሽን፤የዉሃ ሀብት አስተዳደርና የኢነርጂ ዘርፍ ናቸዉ፡፡ተጠሪ ተቋማቱም የኢ.ት/ያ ሜትሮሎጂ እንስቲትዩት፤የኢ.ት/ያ ዉሃ ቴክኖሎጂ እንስቲትዩትና የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጄክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ናቸዉ፡፡

በዚሁ መሰረት በውሃ ሃብት ልማት ዘርፍ ረገድ በዋናነት የውሃና የተፈጥሮ ሃብትን በተቀናጀ መልክ ለማልማት ሀገሪቱ ያላትን ተፋሰሶች መሰረት ያደረገ ጥናት በማጥናት ሁለገብ የተቀናጀ የሃብት አጠቃቀም እንዲኖር ለማስቻል እንደዋና እስትራቴጂ መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ ቀደም ሲል ውሃ ሀብት ላይ ብቻ ያተኮሩ የተፋሰስ ልማት ጥናቶች በተቀናጀና ሁሉንም የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዘርፎች ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ የተፋሰስ ልማቶች ማስተር ፕላን ጥናቶችን የማካሄድ ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍም የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦትን ማስፋፋት፤ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ጥናትና ዲዛይን ማከናወን፤ የግንባታ ቁጥጥር ማከናወን፤ የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሳደግ የሚረዱ የብድር ፈንድ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማሳደግና የብድር ፕሮጀክቶችን አዋጭነት መገምገም ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

በተመሳሳይ በኢነርጂ ልማት ዘርፍም የሃድሮፓወር ቅድመ ጥናትና ዝርዝር ጥናቶችን ማከናወን፤ የታዳሽ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ልማት ማስፋፋት፤ የኢነርጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፤የባዮኢነርጂ ፤የንፋስና ሶላር ሀብቶች ጥናት ማካሄድና ብሄራዊ ኤሌክትሪፊኬሽን ተግባራትን ማከናወን ለበጀት ዓመቱ ከታቀዱት ተግባራት ዋና ዋናዎቹ ስሆኑ በእነዚህ ተግባራት አፈጻጸም ማህበረሰብን፤የግል ባለሀብቱን፤የልማት አጋር ድርጅቶችን ተሳትፎ እና አቅም ግንባታ ማሳደግ የሚችሉ ተጨባጭ ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የተጠሪ ተቋማትን ዋና ዋና ትኩረት መስኮች በተመለከተ የኢ.ት/ያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ወቅታዊ የሆነ የአየር ጠባይ መረጃን ማጠናቀር፤ መተንበይና ማሰራጨት፤የኢ.ት/ያ ዉሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
MINISTRY OF WATER AND ENERGY

በዉሃ ልማት ዘርፍ ለተሰማሩት መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠትና ወጪ ቆጣቢ የመጠጥ ዉሃና ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ እንዲሁም የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ዜጎችን በማስተባበር የታላቁ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ግንባታ ከግብ እንድደርስ አቅም የመፍጠር ሥራዎችን ስሰራ ቆይቷል፡፡

በዚሁ መሰረት ይህ የሪፖርት ሰነድ የሚኒስቴር መ/ቤቱንና በስሩ የሚገኙትን ተጠሪ ተቋማትን የ2014 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በሁለት ክፍሎች በመክፈል እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በክፍል አንድ የውሃ እና ኢነርጂ ሚ/ር መ/ቤት ሪፖርትና በክፍል ሁለት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ የሆኑት ተቋማት የ2014 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖረት ቀርቧል፡፡

ይህ ሪፖርት የክልል ውሃ ቢሮዎችን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ በልማት አጋሮችና በሚ/ር መ/ቤቱ አማካኝነት የተከናወኑና በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን የፊዚካልና የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት እንደመረጃ ምንጭ በዋናነት የተጠቀመ ሲሆን በውስጡም በበጀት አመቱ ተይዘው የነበሩ የትኩረት አቅጣጫዎችን፣ የዘርፉን የበጀት አመቱ አላማና ዝርዝር ግቦችን፣ የዋና ዋና ግቦችንና ትልልቅ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም፣ በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችና የተወሰዱ የመፍትሂ እርምጃዎች እንዲሁም የተከናወኑ የክትትልና ግምገማ ተግባራትን፣ መደምደሚያ፣ ፈታኝ ሁኔታዎችና ወደፊት ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች አካቶ የተዘጋጀ ነው፡፡

## II. የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የ2014 በጀት አመት የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

በ2014 በጀት አመት የስድስት ወራት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የታቀዱና የተከናወኑ ቁልፍ እና አበይት ተግባራት እና የተገኙ ውጤቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

1. **የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በአዲሱ አወቃቀር መሰረት በአራት ፕሮግራሞች የተዋቀረ ሲሆን እነዚህም**

- ፕሮግራም አንድ፡ ሥራ አመራርና አስተዳደር፣
- ፕሮግራም ሁለት፡ ውሃ ሀብት አስተዳደር፣
- ፕሮግራም ሶስት፡ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦት እንዲሁም
- ፕሮግራም አራት፡ ኢነርጂ ልማት ናቸው፡፡

### *1.1 ፕሮግራም አንድ፡ ሥራ አመራርና አስተዳደር፣*

በዚህ ፕሮግራም ስር የሚከናወኑት ተግባራት የአመራርና የድጋፍ አገልግሎት ላይ መሰረት አድርገው በመደበኛ በጀት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፡፡

በፕሮግራሙ ስር በታቀፉት የለውጥ ሥራ አመራር፣ ሴቶች# ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር፣ ግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር፣ ኦዲት፣ ህግ ማማከርና ክትትል፣ አገልግሎቶች አቅርቦት፣ ሰው ሀብት ስራ አመራር፣ ህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን፣ ኢነርጂ መረጃ ጥናትና ልማት ክትትል፣ ጂኦ ኢንፎርሜሽንና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ ፖሊሲና ፕሮግራም ጥናት ክትትልና ግምገማ & የአቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬቶች እና የሥነ ምግባር መከታተያ ጽ/ቤቶች የተለያዩ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ለቁልፍ ፕሮግራሞቹ አጋዥ የሆኑ አበይት መደበኛ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ከተከናወኑት ሥራዎች ዉስጥም ላምሳሌ ለዉጥ ሥራዎች፤-

- የሚ/ር መ/ቤቱ ሠራተኞች የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን በተለያዩ ርእሰ ጉዳዩች ተሰጥቷል
- የሚ/ር መ/ቤቱ እቅድ በአዲሱ አደረጃጀት መሰረት ተከልሏል
- ሪፎርሙን ተግባራዊ ማድረግ እንዲቻል ኮሚቴ ተዋቅሮ ሥልጠና ከወሰዱ ቦኃላ እንደአስፈላጊነቱ ሰራተኞች ግልጽነት እንዲያገኙ ተደርጎ መዋቅሩን ተሰርቷል
- የሰራተኛን መረጃ በICMIS ለማደራጀት ቅድሚያ መረጃ ማጠናከር 95 % ተከናዉኗል
- ድህረ-ገጽ እንደ አዲስ ለማዘጋጀት መረጃ ተሰብስቧል
- የሚኒስቴር መ/ቤቱና የተጠሪ ተቋማት የግቢ ዉበትና ላንድሰኬፕ ዲዛይን ሥራ ተከናዉኗል

በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት በስትራቴጂያዊ፣ የማኔጅመንትና የድጋፍ አገልግሎት መስክ ከአጠቃላይ ዕቅዱ 75.78 በመቶ የሚሆኑት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም፡-**

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት የድጋፍ አገልግሎት መስክ ለሚተገበሩ ለመደበኛ ስራዎች ብር 29.379 ሚ.ሊ ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ ብር 20.614 ሚ.ሊ. (የእቅዱን 70.2%)፡፡

## *1.2 ፕሮግራም ሁለት የውሃ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ*

የውሃና የተፈጥሮ ሃብትን በተቀናጀ መልክ ለማልማት ሀገሪቱ ያላትን ተፋሰሶች መሰረት ያደረገ ጥናት በማጥናት ሁለገብ የተቀናጀ የሃብት አጠቃቀም እንዲኖር ለማስቻል የሚንቀሳቀሰው የውሃ ሀብት አስተዳደር ንዑስ ዘርፍ ግቡን ለማሳካት በ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት የተለያዩ ተግባራትን አከናውኗል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

**ንኡስ ፕሮግራም አንድ የውሃ አጠቃቀምና ፈቃድ አስተዳደር**

- ***ፍትሃዊና አሳታፊ የውሃ ምደባ ማካሄድ፡-*** የውሃ ምደባ ስራ የሚያገለግሉ የግድቦች መረጃዎችን የማደራጀት ተግባር ተከናውኗል፡፡ በአዋሽ ተፋሰስ በሚገኙ ሶስት ግድቦችን መሰረት ያደረገ የውሃ ምደባ ሙሉ በሙሉ ተሰርቷል፡፡ዋና ዋና የውሃ ተጠቃሚዎች ምዝገባ ማካሄድና መረጃን ማደራጀት ስራ ተከናውኗል፡፡
- ***ውሃ የመጠቀም ፈቃድ*** መስጠትና ማደስ፡- ***አዲስ ውሃ የመጠቀም ፈቃድ*** 555 ለመስጠትና ለ 115 እድሳት ለማድረግ በድምሩ 670 አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ385 አዲስና 89 እድሳት በድምሩ 474(62.3 %) ተከናውኗል፡፡
- ***የኮንትራክተሮች አማካሪዎችና ባለሙያዎች*** ፈቃድ መስጠትና ማደስ፡- ለግንባታና አማካሪ ባለሙያዎች 1000 አዲስ 3000 እድሳት በድምሩ 4000 ለመስጠት ታቅዶ ለ742 አዲስ 2483 እድሳት በድምሩ 3225 ተከናውኗል፡፡ በአጠቃላይ በሩብ አመቱ ለድርጅቶችና ባለሙያዎች 5500 እድሳትና አዲስ ብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት ታቅዶ 4316 በማከናወን የእቅዱን 78.47 ፐርሰንት ለማከናወን ተችሏል፡፡

**ንዑስ ፕሮግራም ሁለት የተፋሰስ እንክብካቤና የውሃ አካላት ደህንነት**

- ***የውሃ አካላትን ደህንነት ማስጠበቅ*** የሚችሉ የውሃ አካላት ተፋሰስ ጥበቃ ስራዎችን መደገፍና ማስተባበር፡-በዚህ ተግባር ስር የስነ ህይወታዊ ስራዎች ማከናወንና መንከባከብ፣የውሃ አካለት

ስነ ምህዳር ጥበቃና ልማት በየተፋሰሱ ተስማሚ ችግኝ ተዘጋጅቶ እንዲተከል ማድረግና የስነ አካላዊ ስራዎች ማከናወንና መደገፍ የሚሉ ዋና ዋና ስራዎችን የያዘ ተግባርነው፡፡በዚሁም መሰረት በአዋሽ ተፋሰስ 24 ኩንታል፣ስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ 49 ኩንታል፣እንዲሁም አባይ ተፋሰስ 18.83 ኩንታል የችግኝ ዘርና 202 ኩንታል የችግኝ ማፍያ ፕላስቲክ ተገዝቶ ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በአባይ ተፋሰሰ 9233000 በየተለያዩ ችግኞች ተዘጋጅቷል፤ በተጨማሪም በኦሮሚያ ደቡብ እና አማራ ክልሎች ከባለድርሻ አካላት ጋርበመቀናጀት የችግኝ የጽድቀት መጠን ቆጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡

- **ከአጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የደን እና የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞች ድጋፍና ተከላ ማድረግ-**፡በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ድጋፍ በአማራ 500፣ኦሮሚያ 3000 አዲስ አበባ 10ሺ በድምሩ 13500 ችግኞች ግዥ በመፈጸም ለመትከል በታቀደው መሰረት በኦሮሚያ ገፈርሳና ጀልዱ 3000ሺ የአፕል ችግኞች የመትከል ስራ ተከናውኗል፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለ50 አባዋራ የአፕል እንክብካቤና አያያዝ እንዲሁም የተፈጥሮ ማዳበሪያ አጠቃቀምና አዘገጃጀት ላይ ትኩረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስራ መስራት ተችሏል፡፡
- **የውሃ አካላትን በኢኮ ሃይድሮሎጂ ጽንሰ ሀሳብ መጠበቅ፡-**
    - በአሰላ ቡርክቱ ግድብ ኢኮሀይድሮሎጂ ሰርቶ ማሳያ ጣቢያ  የውሃ ጥራት አመላካች ናሙና ዎች  መሰብሰብ መተንተን በክረምት በበጋና በበልግ በእያንዳንዱ ወቅቱ ሁለት ሁለት ጊዜ በድምሩ 6 ጊዜ ለማከናወን ዕቅድ 47% ለማከናወን ተይዞ 20% ተከናውኗል፣
    - በጅማ ከርጥብ ቡና መፈልፈያ አግሮ ኢንዱስትሪ የሚወጣው ፍሳሽ ማጣሪያ በየሁለት ሳምንቱ አንድ ጊዜ ማጣሪያው ስራ በሚሰራቸው 3 ወራቶች ውስጥ በድምሩ 6 ጊዜ እንዲሁም በቀሪዎቹ 9 ወራት ከማጣሪያው ውስጥ የአፈርና የዕጽዋት ናሙና በበጋ በክረምት ወራቶች አንድ አንድ ጊዜ በድምሩ ሁለት ጊዜ በመሰብሰብ ውጤቱን መሰረት በማረግ ማስተካከያ ስራዎችን ለማከናወን ዕቅድ 30% ለማከናወን ተይዞ አልተከናወነም ያልተከናወነበት ምክንያት በጀት ባለመለቀቁ እና የላቦራቶሪ አገልግሎት የሚሰጠው ድርጅት በግዥ ስርዓት  ባለመለየቱ  ናሙናው አልተወሰደም፡፡
    - በአሰላ  የሚገኘውን አንድ እና ጅማ የሚገኙትን  ሁለት በድምሩ ሶስት ኢኮሀ ሰርቶ ማሳያዎችን  በጨረታ አወዳድሮ ለማስጠገን ዕቅድ 70% ለማከናወን ተይዞ በእቅዱ መሰረት 42.9% ተከናውኗል፡፡

- በጣና ሐይቅ ዳርቻ በዘንዘልማ ቀበሌ ከሚገኘው ሰርቶ ማሳያ( ከዓሳ ገንዳ ውስጥ ፣ ከገንዳው የሚወጣውን ፍሳሽ ተቀባይ ዕጽዋትና ከጣና ሐይቅ ዳርቻ (shoreline) ) የፊዚካል፣ የኬሚካና የስነ ህይወት ናሙናዎች በክረምትና በበጋ አንድ አንድ ጊዜ በድምሩ 2 ጊዜ ለማካሄድ ዕቅድ 50% ለማከናወን ተይዞ በእቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡
- በጉመራ-ርብ ተፋሰስ በደብረ ታቦር ከሚገኘው ኢኮሀ ሰርቶ ማሳያ የአፈር ፊዚካልና ኬሚካል ይዘቶችን የብዝሀ ህይወት ልየታ እና የተመለሱ ስርዓተ ምህዳር አገልገሎቶችን ለመቀመር ዕቅድ 35% ለማከናወን ተይዞ በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት ናሙና መውሰድ ባለመቻሉ ስራው አልተከናወነም፡፡
- በሐዋሳ ወዴሳ ወንዝ ተፋሰስ ላይ ኤዶ ቀበሌ የሚገኘው ሰርቶ ማሳያ ከውሃና ከንጥረነገሮች ኡደት ጋር የተገናኙ የደለል ናሙናዎች የመሰብሰብ የመተንተንና የተመለሱ ስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶችን መቀመር የሚያስችል ስራ ለመስራት 50% ዕቅድ ተይዞ በጀት ባለመለቀቁ ወደ ፊልድ ባለመወጣቱ ምክንያት ተጋባሩ አልተከናዎነም፡፡
- ዓመታዊ የላቦራቶሪ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ተቋም በጨረታ አወዳድሮ መምረጥና ወቅታዊና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠቱን መከታተል 70% በዕቅድ ተይዞ 50 %ተከናውኗል ወይም ከዕቅዱ 71.9% ማከናወን ተችሏል፡፡
- በዩኒስኮ ጥላ ስር የተቋቋመውን የአፍሪካ ኢኮሀይድሮሎጂ ማዕከል ስራ ማስጀመርና ማጠናከር/በጸድቀው የሰው ሀይል መሰረት ጀ.ኢ.ጂ በማዘጋጀትና ማጸደቅ ና ቅጥር በማከናወን ማዕከሉን በሙሉ አቅሙ እንዲሰራ ለማድረግ ዕቅድ 100% ለማከናወን ተይዞ 30% የተከናወነ ሲሆን የግማሽ አመት አፈጻጸሙ 30% ተከናውኗል በመሆኑም ክንውኑ ዝቅ ያለበት ምክንያት መስሪያ ቤቱ ፎሮርም ላይ ስለሆነ ወደ ስራ በሙሉ አቅም አልተገባም፡፡
- በጅማ ከተማ አገራዊ መድረክ በማዘጋጀት የእርጥብ ቡና መፈልፈያ አግሮ ኢንዱስትሪ ፍሳሽ ማጣሪያ ሰርቶ ማሳያን ለሌሎች በዘርፉ ለተሰማሩ መሰል አግሮ ኢንዱስትሪዎች ልምድ እንዲቀስሙ ማድረግ በዕቅድ 20% ተይዞ 20% ተከናውኗል ወይም 100% ተፈጽሟል፡፡
- የውሃ አካላት ዳርቻዎችን ደጀን/በፈር ዞን/ ለመጠበቅ፣ ለማልማትና ለመንከባከብ የህግ ማዕቀፍ/ አዋጅ፣ደንብና መመሪያ/ ዎችን ማዘጋጀት ማጸደቅ እና በየደረጃው ያሉ

ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ግንዛቤ መፍጠር፣ ተግባራዊነቱን መከታተል እንዲሁም እረግረጋማ ቦታዎችን አሁናዊ ሁኔታ መለየትና ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ማድረግ 60% እቅድ ተይዞ በበጀት ምክንያት እና በነበረው ፎርም ስራውን መስራት አልተቻለም፡፡

- የመጨረሻ የሆነውን ባህር ዳር በጣና ሐይቅ ዳርቻ ዙሪያ ያሉ ልማቶችን አሁናዊ ገጽታ (base line ) መረጃ ለመሰብሰብ ዕቅድ 100% ለማከናወን ተይዞ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ተከናውኗል፡፡
- በአገር አቀፍ ደረጃ እንቦጭንና ሌሎች መጤ ወራሪ ዝርያዎችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር የተዘጋጀውን ስትራቴጅክ ዕቅድ ከስነ-ምህዳሮች ጋር በማገናዘብ ተግባራዊ ለማድረግና ለማስፋፋት /በጣና ሐይቅ እምቦጭ በተስፋፋባቸው በተለዩ 5 የሐይቁ እና የወንዞች መገናኛ ቦታዎች ላይ ዝርዝር ዕቅድ ማዘጋጀት ሁለቱን ወደ ተግባር ለማስገባት ዕቅድ 40% ለማከናወን ተይዞ 20% በማከናወን በተያዘው ዕቅድ መሰረት የዕቅዱን 50% ተከናውኗል፡፡
- በአገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ የእምቦጭ ማሰወገድ ስራዎች በስተራቴጂው መሰረት እንዲተገበር ግንዛቤ መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል 40% ታቅዶ በዝዋይ ሀይቅ እና አከባቢው 40% ተከናውኗል፡፡
- የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ በማዘጋጀት በስምጥ ሸለቆና አዋሽ ተፋሰስ ውስጥ ለሚገኙት ለሰፋፊ እርሻዎችና ለሁሉም መስኖ ተጠቃሚዎች የእምቦጭ አረምን የእምቦጭ አረምን አስከፊነት፣ አሰረጫጨቱ ፣ ሊያስፋፉትት የሚችሉ ነገሮች እና ዘለቄታዊ አወጋገዱ ላይ ግንዛቤ መስጠት 40% ታቅዶ በዝዋይ ሀይቅ እና አከባቢው 40% ተከናውኗል፡፡

- **የቤዝን ፕላንና በለድርሻ አካላት ተሳትፎ**

ሚ/ር መ/ቤቱ የተፋሰስ መሪ እቅድ ዝግጅት፣ የተፋሰስ ልማት ትግበራ፣ተቋማትና ማደራጀትና ሚቋቋም፣ስትራቴጂክ እቅድ ዝግጅት፣የበጀት እቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት የውሃ ሃብት አስተዳደርና ልማት ለማሳለጥ አሰፈላጊ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ትኩረት ተደርጎበት እየተሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በዋናነት የሚከተሉት ተግባራት ተከዉኗል፡፡

- የተግባራትና የበጀት እቅድ ማዘጋጀትና ክትትልና ግምገማ ማድረግ፡- በበጀት አመቱ በዘርፉ ሊከናወኑ የታሰቡ ተግባራት የሚከናወኑበትን አግባብ የሚያመለክት የ2014

በጀት አመት የድርጊት መርሀ ግብር የማዘጋጀት እና የሩብ አመቱን እቅድ አፈጻጸም ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር፣ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤትና ለፓርላማ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

- የኦሞ ጊቤ፡-ዋቢሸበሌና የገናሌ ዳዋ ቤዝን ፕላን ማዘጋጀት:
    - በመጀመሪው ስድስት ወራት ተጨማሪ መረጃዎችን የማሰባሰብ ፤
    - ኦሞ ጊቤ፡- በሶስት ቦታዎች ማለትም በአዲስ አበባ ፤ጅማና ጂንካ የባለድርሻ አካላት ውይይት ተካሂዷል ፡፡
    - ገናሌ ዳዋ፡-በአራት ቦታዎች ማለትም በአዲስ አበባ ፤በባሌ ሮቤ ፤በዲላና ጂጂጋ ከተሞች የባለድርሻ አካላት ውይይት ተካሂዷል ፡፡
    - ዋቢ ሸበሌ፡-በሮቤ ከተማ የባለድርሻ አካላት ውይይት ተካሂዷል፡፡በጅጅጋ ፤አዳማና አዲስ አበባ የባለድርሻ አካላት ውይይት ለማካሄድ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- አጠቃላይ የባለድርሻ አካላት ውይይት ማካሄድ ፡- የተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት በማስፈን ሂደት አግባብነት ያላቸው አካላት ያላቸውን ሚና የሚያሳይና በተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ጽንሸ ሀሳብ ላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥና በቀጣይ በጋራ መከናወን ስላለባቸው ተግባራት ለሁሉም ክልሎችና የፌድራል ተቋማት ውይይት ተካሂዷል ፡፡
    - የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ለማሳየት ቅንጅት ለተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር አጠቃላይ የባለድርሻ አካላት ፎረም ተካሂዷል፤
    - በመቀጠልም በ5 ዘርፍ በፌድራል ደረጃ በጋራ መከናወን ስላለባቸው ተግባራት ውይይት ተካሂዷል፤

### *1.3 ንኡስ ፕሮግራም ሶስት፡ የውሃና ኢነርጂ ዘርፍ ምርምርና ስርፀት*

በራስ ኃይልና ከውጭ ተመራማሪዎች ጋር በጋራ በመሆን የሴክተሩን ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማካሄድና እንዲሁም የዘርፉን ዓቅም ግንባታና ውጤት ማጎልበቻ ሥራዎችን በመስራት ዘርፉ ለሀገሪቱ ሶሽዮ-ኢኮኖሚ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ከፍተኛ ጥረትና ዕገዛ በማድረግ ላይ የሚገኘው የውሃና ኢነርጂ ምርምርና ስርፀት ንዑስ ፕሮግራም ስር በ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡-

**በተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደርና ተፋሰስ እንክብካቤ ምርምር ዘርፍ፡**

- የውሃና ኢነርጂ ዘርፍ የጥናትና ምርምር ብሔራዊ የመረጃ ቋት ማዘጋጀትና ሥራ ላይ ማዋል /Development of National Database for Water & Energy Related Researches/ በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 45% ለማከናወን ተችሏል፡፡
- የዋና ዋና ግድቦች ሰው ሰራሽ ሐይቆችን የደለል ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት /Baseline Study of Reservoir Sedimentation in Major Reservoirs in Ethiopia : Causes, Status, Control and Future Course of Action/ በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 30% ለማከናወን ተችሏል፡፡

**በግድብና የሃይድሮፓወር ምርምር ዘርፍ፡**

- የመስኖ እና የመጠጥ ውሃ ግድቦችን ኃይል የማመንጨት ዐቅምን ማጥናት /Power Potential Assessment for Irrigation and Water Supply Dams / በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 30% ለማከናወን ተችሏል፡፡
- የግድቦችን ደህንነት ለመከታተል የሚረዱ መሣሪያዎች ያሉበትን ሁኔታ የሚያሣይ የመጀመሪያ ደረጃ ጥናት / Baseline Study of Dam Instrumentation in Ethiopia: Status, Monitoring and Future Course of Action / በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 30% ለማከናወን ተችሏል፡፡

**በኢነርጂ ሴክተር ምርምር ዘርፍ፡**

- በኢነርጂ ሴክተር ውስጥ ያሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ፈተናዎችን መለየትና ቀጣይ ስተራቴጂዎችን ማጥናት /Opportunities, Challenges and Optimal Strategy for the Energy Sector in Ethiopia/ በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 25% ለማከናወን ተችሏል፡፡

**በመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ምርምር ዘርፍ፡**

- በመጠጥ ውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ሴክተር ውስጥ ያሉ መልካም አጋጣሚዎችንና ፈተናዎችን መለየትና ቀጣይ ስተራቴጂዎችን ማጥናት /Opportunities, Challenges and Optimal Strategy for Urban and Rural Water Supply and Sanitation Services in Ethiopia/ በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 30% ለማከናወን ተችሏል፡፡

**በክሮስ-ሴክቶራልና በሴክተር ድጋፍ ምርምር ዘርፍ፣**

- የእንቦጭ ወረራን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የሚረዱ የአሰራር መንገዶችንና ልምዶችን ማጥናትና ቀጣይ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ /Invasion of Water Hyacinth on Surface Water Bodies of Ethiopia: Evaluation of Control Measures, Practices and Future Course of Action / በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 30% ለማከናወን ተችሏል፡፡
- የግድቦችን ደህንነትና ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት በተመለከተ የግምገማ ጥናት /Dam Safety Review and Construction Management/ ለማካሄድ የታቀደ ቢሆንም ወቅታዊ ጉዳዮችን በመዳሰስ ለኅብረተሰቡ መረጃ ለማድረስ ይቻል ዘንድ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ድርድር ማነቆዎች ትንተና /Deadlock Analysis: Why the Grand Ethiopian Renaissance Dam (GERD) dispute is still unresolved?/ በሚል ርዕስ በግማሽ ዓመት 50% የዝግጅትና የምርምር ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ከዕቅዱ 30% ለማከናወን ተችሏል፡፡
- **ማጠቃለያ** ምርምርና ስርፀት ዳይሮክቶሬት በራስ ኃይልና ከውጭ ተመራማሪዎች ጋር በጋራ በመሆን በቀዳሚነት በተለዩ በስድስት (6) ዋና ዋና የምርምር ዘርፎች ዘጠኝ (9) ችግር ፈቺ የሆኑ አዳዲስ የምርምር ሥራዎችን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት ከታቀደው ዕቅድ የፊዚካል ሥራዎች አፈፃፀም 62.9% ተከናዉኗል፡፡

## ንኡስ ፕሮግራም አራት፡ የግድብ ደህንነት

የግድብ ደህንነት ንዑስ ፕሮግራም ዓላማ በፌደራልና በክልል መንግስታት ለሀይድሮፓወር፣ ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ ዲዛይን የሚደረጉ፣ የሚገነቡትና የተገነቡት ግድቦችን የዲዛይንና ግንባታ ደረጃ እና የድህረ ግንባታ ደህንነት በመከታተል በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት ሳያደርሱ የበለጠ አገልግሎት እንዲሰጡ መመሪያና ደንብ ማዘጋጀት እና የክትትል፣ የቁጥጥርና የአቅም ግንባታ ስራዎችን መስራት የተቋቋመበት አላማ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የ2014 የግማሽ ዓመት የፊዚካልና የፋይናንስ እቅድ ዓፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**የታቀዱና የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- **የ20 ነባር ግድቦች ደህንነት ደሰሳ ጥናት፣** በግማሽ ዓመት የእቅድ አፈጻጸም የነባር ግድቦች ደህንነት ክትትል 8 የግድቦች ክትትል ታቅዶ 2 የተከናወነ ሲሆን ከአጠቃላይ የመደበኛ ሥራ የእቅዱን 18.75 በመቶ ይሸፍናል።

- **የ7 በግንባታ ላይ ያሉ ግድቦች ዲዛይን ክትትልና ቁጥጥር፡** •በግንባታ ላይ ያሉ ግድቦች ደህንነት ክትትል የ3 ግድቦች ክትትል ታቅዶ 1 የተከናወነ ሲሆን ከአጠቃላይ የመደበኛ ሥራ የእቅዱን 8.33 በመቶ ይሸፍናል
- የግድብ ደህንነት ጥናት ፕሮጀክት ተግባራትና ከ ENTRO ጋር በመተባበር የሚዘጋጅ የግድብ ደህንነት ስልጠናና Workshop ተሳትፎና ዝግጅት 1 በመቶ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም ENTRO ባዘጋጀው Development scenarios for coordinated operation of cascade dams in the Eastern Nile inception report ግምገማ ላይ እና Evaluation on expression of interest of Consulting firms ላይ ተሰትፎ ተደርÒል፡፡
- **ማጠቃለያ** ፡- የግድቦች ደህንነት ጥናት ፕሮጀክት ስድስት ወራት አማካይ አፈፃፀም በዕቅዱ መሰረት ሙሉ ለሙሉ ተከናወነ ሲሆን የመደበኛ ሥራዎች ክንውን ደግሞ የእቅዱን 13 መቶ ነው፡፡ አጠቃላይ በአማካይ የንዑስ ፕሮግራሙ አፈጻጸም 56.5 በመቶ ነው፡፡

## ንዑስ ፕሮግራም አምስት፡ የአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ

**ዓላማ-1፡-** በውሃና ኢነርጂ ዘርፍ የሚጠኑና የሚተገበሩ የልማት ፕሮግራሞች ፣ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበረሰብ ጥበቃና ዘላቂ ልማትን መሰረት በማድረግ የህብረተሰቡን ደህንነት፣የሴቶችና ወጣቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ቀጣይነት ያለው ልማት እንዲተገበር ማድረግ፣

**ዓላማ-2፡-** የተፈጥሮ ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ የንጹህ መጠጥ ውሃና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችል የውሃ አቅርቦትን ለተደራሹ ማህበረሰብ ለማቅረብ የሚያስችሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ማህበረሰቡ ለድርቅና በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊደርስ የሚችሉ ችግሮችን እንዲቋቋም ማድረግ፣

**በመተግበር ላይ በሚገኙ የውሃና ኢነርጂ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ልማት እቅድ (Environmental & Social Management Plan) አተገባበርን በመስከ የተደገፈ የክትትልና ግምገማ ቁጥጥር ስራ ከማከናወን አንጻር የተሰራ ስራ፡-**

- ለተለያዩ ፕሮጀክቶች እንደ ልማቱ ዓይነት በመስክ ላይ በመገኘት የክትትልና ግምገማ ስራ ለማከናወን የተለያዩ በውሃና ኢነርጂ ዘርፍ ግምገማ ለማድረግ የሚረዱ ቼክሊስቶች ተዘጋጅተዋል፡፡

- በአሉቶ ላንጋኖ የእንፋሎት ኃይል ማመንጫ፣በአሰላ የንፋስ ኃይል ፕሮጀክት፣በግቤ ሶስት ሀይል ማመንጫ እና በኮይሻ በግንባታ ላይ ያለ ፕሮጀክት ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማ ተካሂዶ ለክቡር ሚኒስትሩ ሪፖርት ተደርጓል፡፡
- የጅማ ከተማ በመጠጥ ውሃና ሳናቴሽን ላይ የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማ ስራ የተከናወነ ሲሆን ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡
- በዝዋይና በሐዋሳ ሀይቆች ላይ የመስክ ክትትልና ግምገማ ስራ የተከናወነ ሲሆን በተለይም የአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ በሚጋባ ተዳሶ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ተዘጋጅቶ ተልኳል፡፡

**የአየር ንብረት ለውጥና የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት (CRGE) የድርጊት ፕሮግራሞችን ማስተባበርና የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን መስራት በተመለከተ፡-**

- የሲአር.ጂ.ኢ. ስራዎችን በመስክ ላይ በመገኘት የክትትልና ግምገማ ስራ ለማከናወን የሚያስችሉ ቼክሊስቶች ማዘጋጀት ተችሏል፡፡
- የሲ.አ.ር.ጂ.አ. አተገባበርን ሊያግዙ የሚችሉ ስራዎች ከተለያዩ አካላት ጋር በመወያየት ሂደቱ የተቃና እንዲሆን ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፣
- በኦሮሚያ ክልል አዳማና አሌልቱ ወረዳዎች፣በሲዳማ ክልል በሶዶሲሚጣና ደሴ ቀበሌዎች፣በሐረሪ ክልል ሶፊና ቡርቃ ቀበሌዎች እና በድሬደዋ ከተማ መስተዳድር በአዳፐቴሽን ፕሮጀክት ስር ለሚከናወኑ የአነስተኛ የመስኖ ውሃ አቅርቦትና የመጠጥ ውኃና ሳኒቴሽን የተሰሩ ተቋማት ላይ በመስክ በመገኘት ፕሮጀክቶቹ የደረሱበትን ሁኔታ፣በአካባቢና በማህበረሰብ ጉዳዮች ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች የተከናውኑ ሲሆን ለሚመለከተው አካልም ሪፖርት ተልኳል፡፡
- በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት በግሪን ክላይሜት ፈንድ/GCF የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ላይ የፕሮጀክት አተገባበርና የአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የክትትልና ድጋፎች ማከናወን ተችሏል፡፡

**የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ ማስተሰረያና ማጣጣሚያ የመነሻ ኃሳቦችና ፕሮፖዛሎች ማዘጋጀትና ለተለዩ የፋይናንስ ምንጮች ማቅረብን በተመለከተ፡-**

- የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ፕሮጀክትን ለመተግበር ይቻል ዘንድ ዝርዝር የአፈጻጸም እቅድ እንዲዘጋጅ የሚያስችል ጥቅል ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን በፕሮጀክቱ ንድፈ ሃሳብ መሰረት በዘንድሮ አመት እንዲተገበሩ የተለዩትን ለመፈጸም የሚያስችሉ ሦስት የመጀመሪያ ረቂቅ ቢጋሮች( 90 በመቶ የተጠናቀቁ) ማዘጋጀት ቢቻልም የአውሮፓ ህብረት

የበጀት ድጎማን የወቅቱን የሀገሪቱ ሁኔታን ምክንያት በማድረግ ገንዘቡ ባለመለቀቁ ቀጣይ ስራዎችን ማከናወን አልተቻለም፡፡

- የታዳሽ ኃይልን በተለየ የፀሃይ ሀይልን በማስፋፋት የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ በተለየ ለመስኖ ልማት እንሰሳ ልማት በቆቦ ጊራና በቦረና ለውሃ አቅርቦት በተለያዩ ጊዜያት የተቆፈሩ የጥልቅ ጉድጓዶችን በፀሃይ ሀይል መስጠትን ታሳቢ ያደረገና በግሪን ክላይሜት ፈንድ/GCF እንዲተገበሩ ለማስቻል ከሲ.አር.ጂ.ኢ. ፋሲሊቲ፣ ጋር በመተባበርና የሚመለከታቸውን የአማራና የኦሮምያ ክልሎች የሚመለከታቸውን በማሳተፍ የአዋጭነትና የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ጥናትና የፕሮጀክት ዲዛይን ዶክመንት ዝግጅት ላይ በማስተባበርና በሙያዊ ተሳትፎ እየተደረገ ይገኛል፡፡
- "Inclusive Green Financing Initiative (IGREENFIN)" ፕሮፖዛል ዝግጅት ላይ እና የታዳሽ ኃይል አቅርቦትን በማስፋፋት የግብርና ውጤቶችን ብክነትን ለመቀነስ እንዲሁም አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ልማትን በማስፋፋት የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋምም ሆነ የማስተሰረይን አላማ ሊያሳካ የሚችል Sustainable Cold Chain ፕሮጀክት ቀረጻ ላይ ተሳትፎ እየተደረገ ይገኛል፡፡

**በውሃና ኢነርጂ ዘርፎች በሚተገበሩ ስራዎች አማካኝነት ሊኖሩ የሚችሉ የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀትና ቅነሳ ልኬት(MRV) ማከናወንን በተመለከተ፡-**

- የቀድሞ አካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳና ልኬትን በሚመለከት ጥናት ያስጠናውን ዶክመንት Report on GHG Mitigation policy assessment for waste management, light transit and Biofuel በመገምገም አስተያየት ተሰጥቷል፡፡
- በቀድሞው በአካባቢ፣ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በአሁኑ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እየተሰራ በሚገኘው የMRV Database ላይ በተዘጋጀው ዓውደ ጥናት ከሚኒስቴር መ/ቤቱ(ከአካባቢና አየር ንብረት ለውጥ ዳይሬክቶሬት) ሦስት ከፍተኛ ባለሙያዎች ተመድበው በኢነረጂው ዘርፍ በ Database ውስጥ መካተት የሚገባቸውን በተመለከተ አስፈላጊውን ግብዓትና አስተያየት መስጠት ተችሏል፣

**የአቅም ግንባታና ቅንጅታዊ አሰራሮችን ማጠናከርን በሚመለከት፣**

- በተለያዩ የማጣጣሚያና የማስተሰሪያ ዓለም አቀፍ የአቅም ግንባታ ስብሰባዎችና ስልጠናዎች በ Virtual Meeting የተካሄደ ሲሆን በሶላር ወተር ፓምፒግ(Solar Water Pumping) ላይ በ GCF ለሚተገበሩ ወደ 60 ለሚደር ለክሎሎችና ለወረዳ ባለሙያዎች በአዳማ ከተማ ስልጠና መስጠት ተችሏል፣
- የMRV እና በአየር ንብረት ለውጥ ድርድር ስርዓትና ድርድር ሂደቶች ላይ በቨርቸዋል በተሰጠ ስልጠና ላይ ተሳትፎ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በCR WASH የተዘጋጀውን የCR WASH መተግበሪያ ማኑዋል ስልጠና ላይ ተሳትፎ የተደረገ ሲሆን ሙያዊና የክፍላችንን የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖ የሚቋቋሙ ፕሮጀክቶች አተገባበር ላይ ልምድ ማካፈል ተችሏል፡፡

**በአየር ንብረት ለውጥ ማስተሰረያና ማጣጣሚያ አለም አቀፍ/ሀገር አቀፍ ፎረሞች፣ስብሰባዎችና ስምምነቶች ላይ መሳተፍን በተመለከተ፡-**

- በአየር ንብረት ለውጥ ማስተሰረያና ማጣጣሚያ አለም አቀፍ/ሀገር አቀፍ ፎረሞች፣ስብሰባዎችና ስምምነቶች ላይ የክፍሉ ሃላፊና ባለሙያዎች በ Virtual Meeting እና እንዲሁም የክፍሉ ሃላፊ በእንግሊዝ በግላስጎ ከተማ በተካሄደው 26ኛው አለምአቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ በጉባኤው ላይ የነበራቸውን ተሞክሮ ለክፍሉ ባለሙያዎች አካፍለዋል፡፡

በአጠቃላይ የ2014 ዓ.ም በጀት ዓመት የመደበኛ የፕሮግራም በጀት የፊዚካል ሥራዎች አማካይ ዕቅድ አፈጻጸም ከታቀደው ከፊዚካል ስራዎች ዕቅድ አንጻር 94 ከመቶ የተከናወነ ሲሆን የካፒታል ፕሮጀክት ክትትል ስራዎች የፕሮግራም በጀት ዕቅድ የፊዚካል አፈጻጸም ደግሞ 66.7 በመቶ ነው፡፡

## ንዑስ ፕሮግራም ስድስት፡ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ

### በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ የተከናወኑ ተግባራት

- በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሙሌት እና የውሃ አለቃቅ መመሪያና ደንብ ላይ የሚደረገው ድርድር እ.ኤ.አ. ኤፕሪል 2021 ዓ.ም. በኪንሻሳ ከተካሄደበኋላ አልተካሄደም፤ የሦስትዮሽ ድርድሩ ቢቋረጥም ሪፖርቱ በሚሸፍነው ጊዜ በጉዳዩ ዙሪያ በርካታ ሥረዎች ተሠርተዋል፡-
- በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዙሪያ በግብፅ፣ በሱዳንና በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ የሃይድሮ ዲፕልማሲና የሚዲያ ዘመቻዎች (ጉብኝቶች፣ምክክሮች፣ የሁለትዮሽና የጉባዔያት መግለጫዎች /ውሳኔዎች፣ የመገኛኛ ብዙኃን ዘገባዎች

/ጽሑፎች፣ወዘተ.) በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ  የድርድርና የምክክር ቡድን ክትትል ተፈትሸዋል፤ምክክር ተደርጎባቸዋል፣

- የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን አስመልክቶ በሚካሄዱ ሁለት ጥናቶች ላይ የግምገማ ሪፖርት ረቂቅ ተዘጋጇል፡፡
- የ ኢትዮጵያ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችና ሃይቆችን የሚመለከት መግለጫ የያዘ ረቂቅ የማብራሪያ ጽሁፍ ተዘጋጅቷል፡፡
- የገናሌ ዳዋ የተፋሰስ ሽፋን የዲጂታ| ኤሊቬሽን ሞዴል  ( DEM ,፣30 meter  resolution ) በቁጥር 27 ከዩናይትድ ስቴስት ጂኦሎጂካል ሰረቬይ (USGS) ከሳተላይ የመረጃ  ምንጭ ተሰብስበቧል (ዳውን ሎድ ተደርጓል)፡፡
- የተፋሰሱን የአፈር አይነት(Soil type ) የሚያሣይ የራስተር መረጃ  ከ FAO ድህረ ገጽ ተሰብስበቧል(ዳውን ሎድ ተደርጓል)፡፡፡
- ከሞዴሉ በመነሳት ካርታዎች (Location map ,slope map)  በጂ አይ ኤስ ተዘጋጅተዋል (የባለሙያተኞች ግምገማ እና ከኢ/ካርታ ሥራ ድርጅት መረጃ ጋር ማመሳከር ወደፊት ይደረጋል)
- የተፋሰሱን የወንዞች ንድፍ (River Network) የሚያሳይ ካርታ  በጂ አይ ኤስ ተዘጋጅተዋል(የባለሙያተኞች ግምገማ እና ከኢ/ካርታ ሥራ ድርጅት መረጃ ጋር ማመሳከር ወደፊት ይደረጋል) ፡፡
- የ2020 የተፋሰሱ የመሬት አጠቃቀም የሚያሳይ ካርታ (Land use) በጂአይኤስ/GIS/ ተዘጋጅቷል፡፡
- የዝግጅት ደረጃው 50% የደረሰ የገናሌ-ዳዋ ወንዝ ተፋሰስን  የአፈር መሸርሸር ሊያሳይ የሚችል የጥናት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል፡፡

በአማካይ የ2014 በጀት ዓመት የስድስት ወራት የውጤት አንድና ሁለት የመደበኛ ስራዎች የፊዚካል አፈጻጸም 93% ነው፡፡

- በድንበርና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳዮች ላይ የተገኘ የምክር አገልግሎት (ፕሮጀክት) በተመለከተ የታለቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የውሃ ሃብት/ሃይድሮ ፓወር ሲሙሌሽን ሞዴልና የወሰን ተሻጋሪ የአካባቢና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም የፕሮጀክቱ አፈጻጸም በ2010 በጀት አመት መጨረሻ በነበረበት የ47% አፈጻጸም ላይ ይገኛል፡፡

## ንዑስ ፕሮግራም ሰባት፡ የተፋሰስ ዕቅድና መረጃ አስተዳደር

**ግቡን ለማሳካት የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

- የመረጃቋት System design document እና System Requirements Specification (SRS)ተዘጋጅተዋል፤ በዚህ መሰረት ተፋሰሶች የመረጃ መረብ የመዘርጋት ሥራ 30% ዕቅድ ተይዞ 25% በመከናወኑ ዕቅዱ 83.33% ተፈፃሚ ሆኗል፡፡
- በውሃ ዘርፍ ለሚካሄዱ 2 የጥናትና ምርምር ስራዎች ድጋፍ ማድረግ፡-ሁለት 2014 ዓ/ም የበጀትአመት የጥናት ርእሶች ተለይተዋል፤ በዚህ መሰረት በውሃ ዘርፍ ለሚካሄዱ 2 የጥናትና ምርምር ለማካሄድ 40% ዕቅድ ተይዞ 10% በመከናወኑ ዕቅዱ 25% ተፈፃሚ ሆኗል፡፡
- ከግርፍ መከላከል ጋር ተያይዞ በአዋሽ ተፋሰስ በጋወኔና ገላአሎ ወረዳዎች በሚ/ር መ/ቤቱ በጀትና አዋሽ ጽ/ቤት ማሽናሪ በመጠቀም የወንዝ መስፋት፤ደላል መጥረግና ወንዝ አቅጣጫ መስቀየር ሥራ ተጀምሯል፡፡

**የአባይ፣ የአዋሽና ስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ የውሃ ኦዲት፡-** በዚህ የካፒታል ፕሮጀክት ተግባር በ3ቱ ልማት ጽ/ቤቶች (አዋሽተፋሰስ፤ አባይ ተፋሰስ እና ስምጥ ሸለቆ ሃይቆች ተፋሰስ) ለሚሰበሰቡ የተፋሰስ መረጃዎች ታልሞ የተዘጋጀ ተግባር ነው፡፡

- አባይ ተፋሰስ ከ40 ወረዳዎች የመስኖ፤ የኢንዳስትሪ፤ የሃይቆች፤ የእንስሳት፤ የውሃ መሰረተ ልማቶች፤ የከርሰ ምድር፤ የወይት ላንድና የሃይድሮ ፓወር መረጃ፤ አዋሽ ተፋሰስ ከ15 ከተማና 14 ወረዳ የመስኖ፤ የኢንዳስትሪ፤ የሃይቆች፤ የእንስሳት፤ የውሃ መሰረተ ልማቶች፤ የከርሰ ምድር፤ የወይት ላንድና የሃይድሮ ፓወርመረጃ እና ስምጥ ሸለቆ ሃይቆች ተፋሰስ ከ8 ከተማና 25 ወረዳ የመስኖ፤ የኢንዳስትሪ፤ የሃይቆች፤ የእንስሳት፤ የውሃ መሰረተ ልማቶች፤ የከርሰ ምድር፤ የወይት ላንድና የሃይድሮ ፓወር መረጃ በታብሌት መረጃ የመሰብሰብ ተግባራት ተከናውኗል፡፡
- ከሶስት ተፋሰሶች የተሰበሰበ መረጃ ወደ ተዘጋጀለት ዳታ ቤዝ ገብቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በውሃ ኦዲት መረጃ ለመሰብሰብ 8% ዕቅድ ተይዞ 7 % በመከናወኑ ዕቅዱ 87.5% ተፈፃሚ ሆኗል፡፡

**በከርሰ ምድር ውሃ ጥናትና ዲዛይን የተከናወኑ ተግባራት**

- በእንግሊዝ መንግስት የሚደገፍ 53 ወረዳዎችን የሸፈነ የከርሰምድር ውሃ ሀብት ጥናት 100% ማጠናቀቅ ታቅዶ ተከናውኗል፡፡
- በአለም ባንክ የሚደገፍ 1 የፕሮጀክት ፕሮፖዛል 85% ማጠናቀቅ ታቅዶ 85%ተከናውኗል፡፡

- በአለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ የከርሰምድር ምድር ውሃን በመጠቀም የአየር ንብረት ለውጥ በውሃ አቅርቦት ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ ለመቋቋም የሚያስችል የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ከባንኩ ባለሙያዎች፣ ከቀድሞው የውሃ ልማት ኮሚሽንና ከመስኖ ልማት ኮሚሽን ጋር በመሆን በመዘጋጀት ላይ ይገኛል።
- ለከርሰ ምድር ውሃ ሀብት ልየታ የሚያስፈልጉ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን የመሰብሰብ እና የማደራጀትሥራ በግማሽ አመቱ ሊከናወን ከታቀደው (50) ሃምሣ ፐርሰንት ሁሉም ተከናውኗል፡፡
- በዩናይትድ አረብ ኤሚሬትስ የገንዘብ ድጋፍ እየተከናወነ ላለው በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች የከርሰ ምድር ውሃ ማውጣት ሥራ ክትትል እና ድጋፍ እየተደረገ ነው።
- በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ሥራ የነበረው የከርሰምድር ውሃ ሃብት ጥናት ዳይሬክቶሬት በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች(ዲላ፣ ሆሳዕና፣ አቃቂ ሆሳዕና፣ ወረኢሉ፣ ከሚሲ ፣ ደብረብርሃን እና ሲዳማ ማፕ ሺቶች) ቀድሞ የጀመራቸውን የከርሰምድር ውሃ ሀብት ካርታ ሥራ በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል።

## በሃይድሮሎጂና ውሃ ጥራት ቁጥጥር የተከናወኑ ተግባራት

- የ145 ሃይድሮሎጂ ጣቢያዎች የውሃ ከፍታ መረጃ መሰብሰብ ታቅዶ 123 በማከናውን 84.82% አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡
- ከሃይድሮሎጂ ጣቢያዎች 175 የውሃ ፍሰት መረጃ መሰብሰብ ታቅዶ 162 በማከናውን 92.57% አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡
- በ9 የሃይድሮሎጂ ጣቢያዎች ላይ የወንዙን/የፕሮፋይል /cross-setion profile/ መረጃ ለመሰብሰብ ታቅዶ በ7 ጣቢያዎች ላይ መረጃዎች በመሰብሰብ የዕቅዱን 77.77% ማከናወን ተችሏል፡፡
- ከሃይድሮሎጂ ጣቢያዎች 140 በወንዝ ላይ የሚጓጓዘው የደለል መጠን መረጃ የሚያሳይ ሳምፕል መሰብሰብ ታቅዶ 140 በማከናውን 95.89% አፈጻጸም ተመዝግቧል፡፡
- የ113 ሀይድሮሎጂ ጣቢያዎች መረጃዎችን ለማጠናቀር ታቅዶ 108 ጣቢያዎች ላይ መረጃዎቹን በማጠናቀር •የዕቅዱን 95.57% ማከናወን ተችሏል፡፡
- በ18 ሀይድሮሎጂ ጣቢያዎች የወንዞች የፍሰት መጠን መተመኛ ግራፍ ወቅታዊ ማድረግና እለታዊ ፣ወርሃዊ፣ አመታዊ የውሃ ፍሰት መረጃ ለማጠናቀር ታቅዶ 4 ጣቢያዎች ላይ መተመኛ ግራፍ ወቅታዊ በማድረግ የመረጃዎቹን ማጠናቀር የተቻለ ሲሆን የዕቅዱን 22.2% ማከናወን ተችሏል፡፡

- 5 አዲስ ጣቢያ እንዲቀቋቋም ተደርጓል፤
- ባሮ እና ኦሞ ጊቤ ተፋሰስ የከርሰ ምድር ውሃ  መረጃዎችን በቁጥር  በመሰብሰብ ለተገልጋዮች በሼፕ ፋይል እና በካርታ ማዘጋጀት ስራ ለመስራት ታቅዶ •የዕቅዱን ማከናወን ተችሏል፤

**መረጃ የማዘጋጀት፤ የመተንተን ስራ፡**

- ለ10 ግድቦች(ቆቃ፤ የከሰም፤ የተንዳሆ፤ የተከዜ፤ የጣና፤ የፍንጫ፤ ነሼ፤ ግልገል ጊቤ I እና III እንዲም የገናሌ III) ጎርፍን ለመከላከል የሚያስችል መረጃ ማዘጋጀትና መከታተል ስራ ለመስራት ታቅዶ •የዕቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፤
- ለ10 ግድቦች የውሃ ሚዛን ስሌት በመስራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመስራት የውሃ አለቃቅ ስርዓት በማውጣት ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ ለባለድርሻ አካላት መረጃው እንዲደርስ ፕረዘንት ተደርጓል፤
- ለመረጃ አሰጣጥ ፖሊሲ ዶክመንት ተዘጋጅቶ በግምገማ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡
- በተፋሰሶች የሃይድሮሎጂ  ጣቢያዎች መረጃዎች ላይ  የጥራት እና የትንተና  ስራ በመስራት ሪፖርት ማዘጋጀት ታቅዶ 50 ፐርሰንቱ ተሰርቷል፤
- የባዚሜትሪ መረጃ መሰብሰብና ሪፖርት ማዘጋጀት ላይ ስልጠና በመስጠት በ4ውሃ አካላት ላይ ለመስራት(ከሚመለከተው ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን) ታቅዶ በበጀትና በወቅቱ ሁኔታ ያልተሰራ ሲሆን በሚቀጥሉት 6 ወራት በ2 የውሃ አካላት  ላይ የሚሰራ ይሆናል፤
- ለ 3 አካላት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠትና ሪፖርት ማቅረብ ስራ ታቅዶ ጋር ስራ ተሰርቷል፡፡ •የዕቅዱን 100% ማከናወን ተችሏል፤
- በጀት ለማፈላለግ የሚረዳ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ማዘጋጀት ስራ ታቅዶ •የዕቅዱን 100 % ማከናወን ተችሏል፤

**የፋይናንስ አፈጻጸም፡-**

**በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ጊዜያት በውሃ ሀብት አስተዳደር ስር ለሚገኙ ንዑሳን ፕሮግራሞች በዕቅድ ለተያዙ መደበኛ ስራዎች እና ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በጠቅላላው ብር 122.47 ሚሊየን ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ አፈጻጸሙም ብር 84.67 ሚሊየን ወይም የዕቅዱን 69.13% ይሆናል፡፡**

### *1.4 ፕሮግራም ሶስት፡ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ዘርፍ*

የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አቅርቦት ዘርፍ የተሰጠውን ሥልጣንና ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው በ2014 በጀት አመት በአንድ ፕሮግራምና በአምስት ንኡሳን ፕሮግራሞች በማዋቀር የፕሮግራሙን አፈጻጸም ስኬታማ ለማድረግ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሠረት በፕሮግራሙ ስር ባሉ አምስት ን/ፕሮግራሞች በበጀት አመቱ በመጀመሪያው ስድስት ወራት የታቀዱና የተከናወኑ ዋና ዋና እና ዝርዝር ተግባራት እንዲሁም የተገኙ ውጤቶች እና የፋይናንስ አጠቃቀም መግለጫ ከማጠቃለያው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

**ሀ. የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ን/ ፕሮግራም**

- የ63 የመጠጥ ውሀ ተቋማት፣ 11% ለማከናወን ታቅዶ 7.34% (የእቅዱን 67%)፤ በፀሐይ ኃይል የሚሰራ የውሀ አቅርቦት ፕሮጀክት የፊዚካል ሥራዎች 42% ለማከናወን ታቅዶ 20.5% (የዕቅዱ 49%) ተከናውኗል፡፡
- በሁለተኛው ምዕራፍ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ለሚገነቡ (3724 የገጠርና 60 የከተማ ውሃ ተቋማት) የቴክኒክ ድጋፎች፣የክትትልና የማስተባበር ስራዎች እንዲሁም የውሃ ዘርፍ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የልማት አጋር ድርጅቶች የማቀናጀትና የማሳለጥ ሥራ 10.8% ታቅዶ 9.3% (የእቅዱን 86%) ተከናውኗል፣
- በመጀመሪያው ምዕራፍ የዋን ዋሽ ፕሮጀክት ሳይጠናቀቁ የቀሩ የ40 ከተሞችና (31 አነስተኛና 9 መካከለኛ) እና 122 የገጠር ባለ ቧንቧ የውሃ ተቋማት ግንባታ ሂደት 0.3% ታቅዶ 0.18% (የእቅዱን 59%) ተከናውኗል
- በበጀት ዓመቱ 21 የተጠናቀቁ የጥናትና ዲዛይን ሰነዶች የፊዚካል ሥራዎች 8.5% ለማከናወን ታቅዶ 1.33% (የዕቅዱ 16%) ተከናወኗል፡፡

**የካፒታል ፕሮጀክቶች**

በዚህ ን/ሮግራም በበጀት አመቱ 3 ፕሮጀክቶች (በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎች የመጠጥ ውሀ አቅርቦት፣የመጠጥ ውሀ አገልግሎት ማስተባበር፣ በፀሐይ ኃይል የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ) የሚተገበሩ ሲሆን የነዚህም የ6 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## 1.4.1 በድርቅ የሚጠቁ አከባቢዎች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት

## 1.4.2 በመንግስት በጀት የሚደገፉ ፕሮጀክቶች

- የዉሃ መገኛ ቁፋሮ በሂደት ላይ የሚገኙ እና የመጨረሻ ዲዛይን የሚቀራችው 3 ፕሮጀክቶች የጥናትና ዲዛይን ዶክሜንቶችን በመገምገም፤ በማበልፀግና የማጠናቀቅ ስራ 20% ለማከናወን

ታቅዶ 6% (የዕቅዱ 30%) የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በአማራ ክልል ሁለት ፕሮጀክቶች( ባቲና መሃምዶ) በጸጥታ ችግር ግንባታቸው በመቆማቸው ነው፡፡

- ለጥናትና ዲዛይን ስራዎች የአማካሪ ግዢ ሂደት ላይ የሚገኙትን 2 ፕሮጀክቶች ጥናትና ዲዛይን ማካሄድና ጥናቱን የመከታተል፣ ዶክሜንቶችን የመገምገም ስራ 20% ለማከናወን ታቅዶ 10% (የዕቅዱ 50%)የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት የአማካሪ ግዢ ሂደቱ በአጽዳቂ ኮሚቴ፣የገምጋሚዎች ኮሚቴ ስራቸው መጓተቱና በግዢ ክፍል ላይ ባለው የስራ ጫና ምክንያት ስላልተጠናቀቀ ነው፡፡
- 16 ፕሮጀክቶችን በአማካኝ ከነበሩበት 13% ወደ 60% ማድረስ (3 በግንባታ ሂደት ላይና 13 በግንባታ ግዥ ሂደት) በ6 ወር ውስጥ 19% ለማከናወን ታቅዶ 12% (የዕቅዱ 61%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም ለገሂዳ፣ደብርና ቦረና በመገንባት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤የግዢ ሂደት ላይ ያሉት (ጉራዳሞሌ፣አዩን፣ዘሀሙሲት፣ጽጽቃ፣ሻፊ...) የመሳሰሉት ግዢ ሂደታቸው ባለመጠናቀቁና የተለያዩ ክፍያዎች (ዋንጌ፣ለገሂዳ፣ቦረና....) በክፍያ መዘግየት ምክንያት አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሆኗል፡፡
- 21 የግንባታ ፕሮጀክቶችን (19 በግንባታና 2 ግንባታ ግዢ ሂደት ላይ የሚገኙትን) በአማካይ 29% ለማከናወን ታቅዶ 20% (የዕቅዱ 69%) የተከናወነ ሲሆን፤ በዚህም በደቡብ ክልል (ፋንታ፣ቶቤ፣ጉዴ-ዲንቢቻ፣ኢራሞ፣ ቶባ ሲያላ፣ ሌሾማዞሪያ፣ ቦንጋና ሃላባ) በግንባታ ላይ ያሉ ቢሆኑም ከነዚህ ውስጥ በክፍያ መዘግየት ምክንያት የተወሰኑት እንዲሁም በአማራ አስ ከተማ፣ሰኞ ገበያ፣ ሳሃል ከተማ፣አልመሃል (ቤንሻንጉል) በጸጥታ ችግር ግንባታቸው በመቆሙ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል፡፡
- በውሃ መገኛ ሥራ ጨረታ ሂደት ላይ የሚገኘዉን አንጋጫ ፕሮጀክት የቁፋሮ ስራ 100 % ማጠናቀቅ 3 የጉድጓድ ተቆፍሮ ተከናዉኖ ለአንድ ጉድጓድ የውሃ ፍተሻ ተደርጓል ሁለቱ ዉሃ በማበልጸግ ሂዳት ላይ ናቸው በዚህም 60% ታቅዶ 50% የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 83% ይሆናል፡፡
- በተለያየ ደረጃ (በጥናትና ዲዛይን፣ጉድጓድ ቁፋሮ እና በግንባታ ሂደት) ላይ ያሉትን 44 ፕሮጀክቶች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ የመስጠት ስራ 50% ለማከናወን ታቅዶ በሁሉም ፕሮጀክቶች ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡

- ከግንባታ ቁጥጥርና ኮንትራት አስተዳደር አማካሪዎች የሚመጡ ሪፖርቶችን የመገምገምና ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ 50% ለማከናወን ታቅዶ ሥራ ሙሉ በሙሉ ማከናወን ተችሏል፡
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጮች የሚቀርቡትን 50 ክፍያዎች በመመርመር ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ በስድስት ወራት ውስጥ 20% ታቅዶ 19% (የዕቅዱ 95%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም (ገልቾት፣ኢራሞ፣ሲያላ፣ሌሾ መዞሪያና ሻሌ፣ ጊዘን) በመመርመር ለሚመለከተው ክፍል ማስተላለፍ ተችሏል፡፡
- በአየር ንብረት ለውጥ በመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና ሐይጅን ላይ ያለውን ተጽዕኖ ዙሪያ ለ30 ግለሰቦች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ30 ግለሰቦች (ለ5 ሴቶችና ለ 25 ወንዶችን) የዕቅዱ 100% በDCR-WASH ተከናውኗል፡፡
- የግንባታ ቁጥጥር ቢጋር ማበልጸግና ማዘጋጀት 5% ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ በዚህም የኦንጎጊና ጋምቤላ ከተማ፣ ዳዬና ጨለለቅቱ፣ጀልዴሳ እና አሳይታ-አፋንቦ ቢጋሮች እንዲበለፅጉ ተደርጓል፡፡
- በአጠቃላይ በመንግስት በጀት ከሚገነቡት ፕሮጀክቶች መካከል የሀላባ በሸኖ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በከፊል ተጠናቆ 22,000 (11,220 ሴቶች) ህብረተሰብ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

### 1.4.3 በCWA-II (Consolodated WaSH Account-II) በጀት የሚደገፉ ፕሮጀክቶች

- በጥናትና ዲዛይን ላይ የሚገኙ 8 ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ዶክሜንቶችን በመገምገምና በማበልፀግ የማጠናቀቅ ስራ 40% ለማከናወን ታቅዶ 30% (የዕቅዱ74%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን የቦዳሌ, ሂግሎሪ, ጫሪቲ- ሃርገሌ, ፊልቱ-ዶካ ሶፍቱ እና ዳሊፋጊ ፕሮጀክቶችን ጥናትና ዲዛይን ዶክሜንቶችን የመገምገም ስራ ተሰርቷል፡፡
- 6 የግንባታ ፕሮጀክቶችን (1 በግንባታ ሂደት ላይና 5 በግንባታ ግዥ ሂደት) በአማካኝ 8% ለማከናወን ታቅዶ 3% (የዕቅዱን 35%) ተከናውኗል፡፡ በዚህም ከ6 ፕሮጀክቶች ውስጥ የሳንኩራን የግንባታ ከ5.2 ወደ 22% በማድረስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆን ዋናው ምክንያት አዩን፣ጉራዳሞሌ፣ዘሀሙሲትና አሳይታ አፋምቦ የግንባታ ግዢ ሂደት ስላልተጠናቀቀ ነው፡፡
- ለ4 የውሃ መገኛቸው ያልተረጋገጠላቸው ፕሮጀክቶቹን (ዳሮለቡ፣ሀመርና በና፣አፍዴራና ኤረር) ወደ ጨረታ ሂደት ውስጥ ማስገባትና የቁፋሮ ስራ የማጠናቀቅ ሂደት 30% ለማከናወን ታቅዶ 10%(የዕቅዱ 33%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም አፍዴራ በጸጥታ ምክንያት ሲዘገይ፣

የተቀሩት የግገር ሂደታቸው በአጽዳቂ ኮሚቴ፣የገምጋሚዎች ኮሚቴ ስራቸው መጓተቱና በግገር ክፍል ላይ ባለው የስራ ጫና ምክንያት ስላልተጠናቀቀ ነው፡፡

በተለያየ ደረጃ (በጥናትና ዲዛይን፣ጉድጓድ ቁፋሮ እና በግንባታ ሂደት) ላይ ያሉ 40 ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረመልስ የመስጠት ስራ 51% ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን፤ በዚህም የሳንኩራ፣ሃመር በና፣ ሀዋሳ ዙሪያ፣ሲራሮ፣ምእራብ አባያ፣ ቡረጂ፣ ኮንሶ፣ጠንባሮ፣ዛላ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ መልስ ተሰጥቷል፡፡

- ከግንባታ ቁጥጥርና ኮንትራት አስተዳደር አማካሪዎች የሚመጡ ሪፖርቶችን በመገምገም ግብረመልስ የመስጠት ስራ 51% ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሙሉ ለሙሉ ተከናውኗል፡፡በዚህም ሳንኩራና ኦንጎጊ ሪፖርቶች ታይተዋል፡፡
- ከአማካሪና ከስራ ተቋራጭ የሚቀርብ 13 ክፍያዎችን በመመርመር ለሚመለከተው ክፍል ለማስተላለፍ ታቅዶ 4 የሱማሌ ክልል ፕሮጀክቶችን (ቦደሌና ሂግሎሌ፣ቻረቲ ሀረገሌ ፊልቱ ዴካ ሶፍቲ) በመመርመር ማስተላላፍ ተችሏል፡፡
- በአመት ሁለት ጊዜ ባለድርሻ (ለ50 ተሳታፊዎች) አካላት ጋር የስራ አፈጻጸም ግምገማና የምክክር አውደ ጥናት ማካሄድ 30% ለማከናወን ታቅዶ የግምገማና የምክክር አውደ ጥናት በማካሄድ ሙሉ ለሙሉ እቅዱን ለማከናወን ተችሏል፡፡
- በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 6 ወራት በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት 11% ለማከናወን ታቅዶ 7.34% (የእቅዱን 67%) ተከናውኗል፡፡

### 1.4.4 የመጠጥ ውሃ ማስተባበር ፕሮጀክት

**የመጀመሪያው ምዕራፍ አንድ ዋሽ ማስተባበር ስራዎች**

**<u>የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት</u>**

**ሀ. <u>የመካከለኛ ከተሞች</u>**

## ሠንጠረዥ 1፡ የ7 መካከለኛ ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ያሉበት ደረጃ

| ተ.ቁ | ክልል | በግንባታላይየሚገኙ | | | | የተጠና ቀቁ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ≥90% | ≥75% - <90% | ከ≥50% - <75% | ከ50% በታች | | |
| 1 | ኦሮሚያ | በደኖ (97%)<br>ስሬ (98%)<br>ሀሳሳ (95%)<br>ሰንዳፋ በኬ (94%) | ጎቤሣ (88.30%) | | ሮቤ (38%) | | የስሬ ከተማ አንድ ጀኔሬተር በመጠቀም በከፊል አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ |
| 2 | ደቡብ | | | | ጨንቻ (31%) | | የጨንቻ ከተማ የመጨረሻው የጥናት እና ዲዛይን ሰነድ በመሃንዲሶች እየተገመገመ ሲሆን በሚመለከተው አካል/ላት የበጀት ውሳኔ ወይም ይሁንታ ካገኘ በቀጣይ የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት አየር ላይ እንደሚውል ይጠበቃል፡፡ |
| ድምር | | 4 | 1 | | 2 | | |

- በበጀት ዓመቱ ግማሽ አመት በኦሮምያ ክልል የስሬ መካከለኛ ከተማን በከፊል በማጠናቀቅ 20,487 (10,400 ሴት) ነዋሪዎች የንፁህ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

## ለ. የአነስተኛ ከተሞች

**ሠንጠረዥ 2፡-የ15 አነስተኛ ከተሞች የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶች ያሉበት ደረጃ**

| ተ.ቁ | ክልል | በግንባታ ላይ የሚገኙ | | | የተጠናቀቁ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | >90% | ከ75% - 90% | ከ50-75% | | |
| 1 | ኦሮሚያ | ገባሮቢ(95%)፣ አዱላላ (96.69)% | | ያዮ (67.75%) | ኢንጪኒ፣ ጫንቃ ፣ሚኤሶ | የገባሮቢ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በከፊል ተጠናቆ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል |
| 2 | አማራ | አምባ ጊዮርጊስ (97.5%)፣ አጅባር አምባማሪያም (95%)፣ ቆላድባ (98%)፣መንታ ውሃ (93%) | ደጎሎ (87%) | ረቡዕ ገበያ 65% ፣ ወይንውሃ 52% | | |
| 3 | ደቡብ | | እምድብር (80%) | | ማሬ | |
| ድምር | | 6 | 2 | 3 | 4 | |

- በኦሮሚያ 3 አነስተኛ ከተሞች (ኢንጪኒ፣ ሚኤሶ እና ጫንቃ) እንዲሁም በደቡብ 1 አነስተኛ ከተማ (ማሬ) ሙሉ በሙሉ ተጠናቀው ለ69,537 (36,000 ሴት) ነዋሪዎች የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡

ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
MINISTRY OF WATER AND ENERGY

## የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት

- በክልሎች እየተገነቡ ያሉና ያልተጠናቀቁ 122 ባለ ቧንቧ የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ ላይ ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ማድረግ 10% ለማከናወን በታቀደው መሠረት 10% ተከናውኗል፡፤ በዚህም በአማራ ክልል 1 ፕሮጀክት (በሰሜን የገሪገራመባ ፕሮጀክት) ተጠናቆ 2,962 (1,500 ሴት) የህብረተሰብ ክፍል ፣ በኦሮሚያ (ምእራብ ሀረርጌ ሀቀንጅራታ፣ምእራብ ጉጂ ኢጀርሳ፣ምስራቅ ባሌ ሀሪሮ፣ቡኖ በደሌ ቆሎ ሲሬ፣ ኤሉ አባቦራ አጋታ ቂጣቢሽ፣ምስራቅ ሸዋ ጎቢኖ ጉቢሳ) ተጠናቀው 28,561(14,566 ሴት) የህብረተሰብ ክፍል የንጹህ መጠጥ ውሀ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ በአጠቃላይ ክልሎች ትግበራ በተጠናቀቁ 7 ፕሮጀክቶች 31,523 ዜጎች (16,066 ሴቶች) የንጹህ መጠጥ ውሀ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡
- በአጠቃላይ ግንባታቸው ሙሉ በሙሉ በተጠናቀቁ በፌደራል 3 አነስተኛ ከተሞች እና 7 በክልሎች የተተገበሩ እንዲሁም በከፊል በተጠናቀቀ 1 መካከለኛ ከተማ በድምሩ በ11 ፕሮጀክቶች 121,547 ዜጎች (62,466 ሴቶች) የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡
- በአጠቃላይ በመጀመሪያው ምዕራፍ የዋን ዋሽ ፕሮጀክት ሳይጠናቀቁ የቀሩ የ40 ከተሞችና (31 አነስተኛና 9 መካከለኛ) እና 122 የገጠር ባለ ቧንቧ የውሃ ተቋማት ግንባታ ሂደት 0.3% ታቅዶ 0.18% (የእቅዱ 60%) ተከናውኗል፡፡

### ሁለተኛ ምዕራፍ ዋሽ ማስተባበር ስራዎች

### የከተማ መጠጥ ውሃ ሥራዎች

- በበጀት አመቱ ከክልሎች የሚቀርቡ የ11 አነስተኛ እና መካከለኛ ከተሞች የመጠጥ ውሃ ጥናትና ዲዛይን ሰነዶችን ገምግሞ የማበልፀግ ስራ ከታቀደው ውስጥ በ6 ወራት 45% ለማከናወን ታቅዶ 9.1% (የዕቅዱ 20.2%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም በሶማሌ ክልል (የዋርደር ከተማ) የጥናት ሰነድ የማበልፀግ ስራ ተሰርቷል፡፡አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ክልሎች (ሲዳማ፣አፋር፣ጋምቤላ) እንደታቀደው የጥናት ሰነድ አጠናቀው ባለመላካቸው ነው፡፡
- በከክልሎች የሚላኩ 13 የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች የጨረታ ሰነዶች መገምገምና ማበልጸግ የታቀደ ሲሆን ከታቀደው 33% በሶማሌ ክልል (የዋርደር ከተማ) የጨረታ ሰነድ በመገምገም የዕቅዱን 8% ለማከናወን የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ 23.31% ነው፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ክልሎች (ሲዳማ፣አፋር፣ጋምቤላ) እንደታቀደው የጥናት ሰነድ አጠናቀው ወደ ጨረታ ሰነድ ዝግጅት ባለመግባታቸው ነው፡፡
- 56 አነስተኛ እና 8 መካከለኛ ከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶችን 40 ዙር በጥናት፣ዲዛይን፣በግንባታ ክትትል፣በፕሮጀክት አስተዳደር ድጋፍ መስጠት 50% ለማከናወን

ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
MINISTRY OF WATER AND ENERGY

ታቅዶ በመስክ ደረጃ በሶማሌ ክልል የዋርዴር እና የሽላቦ ከተሞችን፣ በኦሮምያ ክልል የአሊዶሮ ከተማን እንዲሁም በሌሎች ክልሎች በተለያዩ የግንኙነት መንገዶች የክትትልና ድጋፍ በማድረግ 40% በማከናወን የዕቅዱን 80% ማድረስ ተችሏል፡፡

- የከተሞች መጠጥ ውሃ ፕሮጀክት አካል የሆኑ የሳኒቴሽን ፋሲሊቲ ስራዎች ላይ በየደረጃው ከሚመለከተው አካል ጋር ቴክኒካዊ (በዲዛይን፣ ግንባታና በዶክመንት ዝግጅት) ድጋፍና ክትትል ለማድረግ 50% የታቀደ ሲሆን በአፋር ክልል፣ በሶማሌ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ከጥናት እና ዲዛይን ጋር ተያይዞ የቅርብ ድጋፍና ክትትል በማድረግ 40% በማከናወን አፈጻጸሙም 80% ተችሏል፡፡

## አነስተኛ ከተማ

- በሶማሌ 1 አነስተኛ ከተማ (ሽላቦ) ተጠናቆ ለ 10,111 ነዋሪዎች (5,100 ሴቶች) የንፁህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡
- **ሠንጠረዥ3፡የምዕራፍ ሁለት የከተሞች መጠጥ ውሀ አቅርቦት ያሉበት ደረጃ**

| ክልል | የከተማ አይነት | የከተማ ብዛት | የቅድመ ግንባታ መሰፈርቶችንበመሟላት ላይ | የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ | በተለያዩ የጨረታ ሂደት ላይ | በግንባታ ላይ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኦሮሚያ | መካከለኛ | 4 | - | 2 | - | 2 | ለገባሮ እና ያቤሎ የቅድመ ዝግጅት መስፈርት ሰነዶች ተልከው ይሁንታ (No Objection) እየተጠበቀ ይገኛል፡፡<br>የፊንጫዋ (6.12%) ከተማ የግንባታሥራ ተጀምሯል<br>የወሊሶ(5%) ከተማ የግንባታ ሥራ ተጀምሯል |

| ክልል | የከተማ አይነት | የከተማ ብዛት | የቅድመ ግንባታ መሰፈርቶችንበመሟላት ላይ | የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ | በተለያዩ የጨረታ ሂደት ላይ | በግንባታ ላይ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አነስተኛ | 13 | 8 | - | 3 | 2 | ጋጣ እና ሃሮዋጩ፡ ለሲቪል ስራዎች ግንባታ በድጋሚ ጨረታ ለማዉጣት የባንኩን ይሁንታ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል ቶሬ (17.5%) እና አሊዶሮ (35%) የግንባታ ሥራ ተጀምሯል ቢሎ ቁፋሮ ለማከናወን በዝግጅት ላይ (Rig Mobilization)፡፡ኑኑ የቁፋሮ ስራ (100%) ተጠናቋል፡፡ ሸቦቃ በቁፋሮ ላይ ይገኛል ( 35%)፡፡ቤላሚ የቁፋሮ ስራ (100 %) ተጠናቋል፡፡ ሶፎመር እና ሃዳ፡ የቁፋሮ ስራ የኮንትራት ውል ተፈርሟል ኩርፋ ጨሌ እና ዘምባባ፡ ለቁፋሮ ስራ የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይኢናንጎ፡ ለሲቪል ስራዎች ግንባታ በድጋሚ ጨረታ ለማዉጣት የባንኩን ይሁንታ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል |
| ደቡብ | መካከለኛ | 4 | - | | - | 4 | የተርጫ ከተማበግንባታ ላይ ሲሆን አፈፃፀሙም 25% ላይ ይገኛል፡፡የሳውላ ከተማ በግንባታ ላይ ሲሆን አፈፃፀሙም 19% ላይ ይገኛል፡፡የዲላ ከተማ በግንባታ ላይ ሲሆን |

| ክልል | የከተማ አይነት | የከተማ ብዛት | የቅድመ ግንባታ መሰፈርቶችንበመሟላት ላይ | የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ | በተለያዩ የጨረታ ሂደት ላይ | በግንባታ ላይ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | አፈፃፀሙም 26% ላይ ይገኛል፡፡የወራቤ ከተማ በግንባታ ላይ ሲሆን አፈፃፀሙም 15% ላይ ይገኛል፡፡ |
| | አነስተኛ | 2 | | | 1 | 1 | የማሻ ከተማ ፡ ጨረታው በድጋሚ አየር ላይ ውሎ የጨረታ ሰነድ እየተሸጠ ይገኛል፡፡የጊዶሌ በግንባታ ላይ ሲሆን አፈፃፀሙም 17% ላይ ይገኛል፡፡ |
| ቤ/ጉሙዝ | አነስተኛ | 2 | | | 2 | | የዶቢ ከተማ ውለታ ተፈርሟል፡፡ በፀጥታ ምክንያት ምንም አይነት እንቅስቃሴ የለምየዳለቲ፡ ከተማ በድጋሜ ጨረታ ለማውጣት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ |
| ጋምቤላ | አነስተኛ | 4 | 4 | | | | የአራቱም ከተሞች አማካሪ ድርጅቱ የመጀመርያውን ረቂቅ የጥናት ሰነድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ |
| ሶማሌ | አነስተኛ | 2 | | | 1 | 1 | የሽላቦ ከተማ 100% ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል ፡፡<br>የዋርደር ከተማ የኮንትራት ውል ተፈርሞ ለኮንትራክተሩ ቅድመ ክፍያ የተከናወነ |

| ክልል | የከተማ አይነት | የከተማ ብዛት | የቅድመ ግንባታ መሰፈርቶችንበመሟላት ላይ | የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ | በተለያዩ የጨረታ ሂደት ላይ | በግንባታ ላይ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አማራ | አነስተኛ | 20 | 2 | 3 | 3 | 5 | የመርሳ ከተማ ግንባታ 50.45% ( በፀጥታ ችግር ባለበት ቆሟል) ፣የጊሽ አባይ ከተማ ግንባታ 52%፣ የአዘና ከተማ ግንባታ 73.13% እና መኮይ ከተማ ግንባታ 47.90% ፣ ጫጫ ከተማ ግንባታ 51.69% ላይ ደርሰዋል፡፡<br>ጊሽራቤል፣ ሃርቡ እና ሰኞ ገበያ ፡ ከተሞች እንደገና ጨረታ ለማውጣት ሰነዱ ይሁንታን ያገኝ ዘንድ ወደ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የተላከ ሲሆን ሰነዱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የግዥ ክፍል ባለሙያዎች እየታየ ይገኛል፡፡ጫጫ ከተማ የኮንትራት ውል ተፈርሞ ሳይት ርክክብ ተደርጓል፡፡ የለሚ፣ወይን አምባ እና ዱርቤቴ የጨረታ ሰነድ ኤር ላይ ውሎ እየተሸጠ ይገኛል፡፡ ሁለት ከተሞች (ወገዳ እና ማህደረ ማርያም) በቅድመ መስፈርት በማሟላት ላይ<br>ሰባት ከተሞች (ሺንፋ፣አለም ከተማ፣ አረርቲ ፣ጢስ አባይ ፣ማህደረ ሰለም ፣ አብርሃጅራ እና ገበዘ ማርያም ) በተያዘው በጀት አመት አልታቀዱም |
| አፋር | አነስተ | 2 | 1 | | 1 | | የኮነባ ከተማ፡ የሲቪል |

| ክልል | የከተማ አይነት | የከተማ ብዛት | የቅድመ ግንባታ መሰፈርቶችንበመሟላት ላይ | የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ | በተለያዩ የጨረታ ሂደት ላይ | በግንባታ ላይ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ኛ | | | | | | ግንባታ ጨረታ የግምገማ ሪፖርት ተጠናቆ ወደ ውሃና ኢነርጂ ሚንስቴር ግዥ ክፍል ለይሁንታ የተላከ ሲሆን የቀረበው ሰነድ በመታየት ላይ ይገኛል፡፡ጭፍራ ከተማ የቅድመ ዝግጅት መስፈርት ከሆኑት አንዱ የሆነው የውሃ መገኛ ማረጋገጥ ስራ ሲሆን ለከተማው የውሃ ቁፋሮ በመከናወን ላይ ይገኛል ስለሆነም ወደ ቀጣይ የትግበራ ደረጃ መሻገር አልቻለም፡፡ |
| ሲዳማ | አነስተኛ | 3 | | 3 | | | የ 3ቱም (ወንዶ ባሻ፣ሃዌላ እና መጀ) ከተሞች ለቁፋሮ ስራ የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡ |
| ድምር | መካከለኛ | 8 | - | 2 | 1 | 5 | 8 |
| | አነስተኛ | 56 | 15 | 6 | 10 | 10 | 41 |
| | ጠቅላላ | 64 | 15 | 8 | 11 | 15 | አጠቃላይ 49 ከተሞች በበጀት አመቱ የታቀዱ ሲሆን በአማራ ክልል 7 ከተሞች አልታቀዱም፣እንዲሁም በትግራይ ክልል 8 አነስተኛ ከተሞች በጸጥታ ችግር ምክንያት አልታቀዱም፡፡ |

**የገጠር መጠጥ ውሃ ስራዎች**

- በክልሎችና በአማካሪ የሚቀርቡ የገጠር መጠጥ ውሃ ተቋማትን የጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶችና ሌሎች ተመሳሳይ 32 ሰነዶችን መገምገምና ማበልፀግ በስድስት ወራት 40% ታቅዶ ከእቅድ በላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡
- ክልሎች ከበOWNP-CWA II የትግበራ ማንዋል መሰረት እንዲፈጽሙና አስፈላጊ የፕሮጀክት ትግበራ ዝግጁነት Readiness criteria/ እንዲያከናውኑ ድጋፍ ማድረግና መከታተል 40% ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን በጥናትና ዲዛይን፣በግንባታ ክትትልና በፕሮጀክት አስተዳደር ለክልሎች፣በፕሮግራሙ በታቀፉ ወረዳዎች 44 ጊዜ በመስክ ላይ የቴክኒክ ድጋፍ የመስጠት ስራ 40% ለማከናወን ታቅዶ 27%(የዕቅዱ 68%) ተከናውኗል፡፡ በዚህም ቤሻንጉል(ካሻፍ)፣ በሶማሌ ለ21 ወረዳዎች፤ ሲዳማ 10 ወረዳዎች እና ደቡብ ኦሞ ዞን ሁለት ወረዳዎች የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡
- በአጠቃላይ የምዕራፍ ሁለት የማስተባበር ፕሮጀክት የፊዚካል ሥራዎች 10.8% ለማከናወን ታቅዶ 9.3% (የዕቅዱ 86%) ተከናውኗል፡፡

**በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ የገጠር የመጠጥ ውሃ ተቋማት ፕሮጀክት**

- 5 በጸሐይ ኃይል የሚሰሩ አገር ውስጥ የገቡ የግንባታ እቃዎች የጥራት ፍተሻ (materials inspection)፣ የውሃ ተቋማት ግንባታ መከታተልና ድጋፍ ማድረግ (በጃፓን ኤምባሲ እርዳታ የሚሰሩ ፡- በአፋር ክልል 3ና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል 2) 40% ለማከናወን ታቅዶ 10% (የዕቅዱ 25%) ማከናወን የተቻለ ሲሆን በዚህም የግንባታ እቃዎች በማስገባት ወደ መስሪያቤቱ መጋዘን ማስቀመጥ ተችሏለል፡፡ ከፀጥታ ችግር ጋር በተያያዘ ስራው ስለቆመ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡
- በታዳሽ ኢነርጂ ሀይል የሚሰሩ የመጠጥ ውሃ ተቋማትን ኢምፓክት (Impact Evaluation) ለማስገምገም የአማካሪ ቅጥሩን በማጠናቀቅና ትግበራውን የመከታተልና የመገምገም ስራ 40% ለማከናወን ታቅዶ 20% (የዕቅዱ 50%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም የጨረታ ሂደቱ ተጠናቆ ውል የተገባ ቢሆንም አማካሪው የተለያዩ ፈቃዶችን እስኪያድስ ስራው ተጓቷል፡፡
- ጥናታቸው ለተጠናቀቁ ተቋማት ለግንባታ ማስፈጸሚያ የሚውል ፈንድ የማፋላለጊያ አንድ ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ለማዘጋጀት በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ፈንዲንግ ኤጀንት ተልኳል፡፡

- 25 የፀሃይ ኃይል የመጠጥ ውሃ ተቋማት ግንባታ የመከታተል ስራ 30% ለማከናወን ታቅዶ 15% (የዕቅዱ 50%) ተከናውኗል፡፡በዚህም የስድስት የመጠጥ ውሃ ተቋማቶች (ደቡብ ክልል 3፣ ኦሮሚያ 3) የሰፖርት ስትራክቸር (የሲቪል ስራዎች) የተጠናቀቀ ሲሆን፣የ25 ሳይቶች ከውጭ የሚገቡ እቃዎች ማስገባት ተችሏል፡፡ በአማራና ትግራይ በፀጥታ ችግር ምክንያት ስለቆመ አፈጻጸሙ ዝቅ ሊል ችሏል፡፡
- በጄኔሬተር የሚሰሩ 10 የመጠጥ ውሃ ተቋማትን ወደ ፀሃይ ኃይል ለመቀየር በራስ አቅም ጥናትና ዲዛይን ስራ 35% ለማከናወን ታቅዶ 5% (የዕቅዱ 14%) ተከናውኗል፡፡ ይህም የጥናት ቢጋር (ToR) ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን ወቅታዊ የፋይናንስ ችግር በማጋጠሙ ምክንያት በመስክ ተገኝቶ ስራውን ማከናወን ባለመቻሉ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል፡፡
- በጄኔሬተር የሚሰሩ 17 የመጠጥ ውሃ ተቋማት ወደ ፀሃይ ኃይል በራስ አቅም እንዲቀየሩ ድጋፍ የማድረግ ስራ (በአማራ፤በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች) 20% ለማከናወን ታቅዶ 10% (የዕቅዱ 50%) ተከናውኗል፡፡ በዚህም የ12 ሳይቶችን ማቴሪያል በመስክ ላይ ፍተሻ ስራ እንዲሁም የአንድ ተቋም ተከላ ስራ ተከናውኗል፡፡ ወቅታዊ የፋይናንስ ችግር በማጋጠሙ ምክንያት በመስክ ተገኝቶ ስራውን ማከናወን ባለመቻሉ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል፡፡
- በየክልሉ የሚገኙ በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ የመጠጥ ዉሃ ተቋማቶችን መረጃ መሰብሰብ በመረጃ ቋት የማደራጀት ስራ 40% ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙለኩ ተከናውኗል፡፡
- 
- በአጠቃላይ በፀሐይ ኃይል የሚሰራ የውሀ አቅርቦት ፕሮጀክት የፊዚካል ሥራዎች 42% ለማከናወን ታቅዶ 20.5% (የዕቅዱ 49%) ተከናውኗል፡፡

**በብሪቲሽ ኢምባሲ የፋይናንስ ድጋፍ የሚከናወን የአየር መዛባትን የሚቋቋም የመጠጥ ውሃ አቅርቦት (DCR-WASH)**

- የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን መመሪያዎች ፤ማናዋሎችና መስፈርቶች የCR- WaSH መርሆችን እዲያካትቱ ማድረግና መከታተል በስድስት ወራት ውስጥ 60% ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡
- ዘጠኝ የዲዛይን ሶፍትዌሮች እና የግንባታ አስተዳደር ስልጠናዎችን 230 ባለሙያዎች ስልጠና መስጠት 138 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታስቦ ለ101 ባለሙያዎች (የዕቅዱን 73%) ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የፕሮግራሙን ስራዎች መደገፍ፣መከታተል እና ማስተባበር በስድስ ወራት ውስጥ 60% ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡ በዚህም ገንዘብ ወደ ክልሎች እንዲላክ እቅድን መከለስ፣ WSP ስራዎችን ማስተባበር ተከናውነዋል፡፡
- ፕሮግራሙን በተለያየ ደረጃ የማስተዋወቂያ የጋራ ምክክር መድረክ ማዘጋጀት በስድስ ወራት ውስጥ 60% ታቅዶ ስልጠና በተሰጠበት ወቅት ጎን ለጎን ፕሮግራሙን የማስተዋወቅ ስራሙሉ ለሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ለ. በሳኒቴሽን መሰረተ ልማት አቅርቦት ን/ ፕሮግራም**

**የካፒታል ፕሮጀክቶች**

በዚህ ፕሮግራም ስር 2 ፕሮጀክቶች (የ23 ከተሞች የፍሳሽ ማስወገጃ ተቋማት ግንባታ እና ከአይነ ምድር የፀዳ አካባቢ ፕሮጀክቶች) የሚተገበሩ ሲሆን የነዚህም የዕቅድ አፈፃፀም ቀጥሎ ቀርቧል፡-

1. **የ23 ከተሞች የፍሳሽ ማስወገጃ ተቋማት ፕሮጀክት**

- **የ5 ከተሞች (ባህርዳር፣ ሃዋሳ፣ አዳማ መቀሌ እና ድሬዳዋ) የተቀናጀ የከተማ አቀፍ የሳኒቴሽን መሰረተ ልማት ግንባታ ወደ 25% በማድረስ፡-**
  - የግንባታ ክትትል ተቆጣጠሪ አማካሪ ቅጥርን አሁን ካለበት 84% ወደ100% ማድረስ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 16% ለማከናወን ታቅዶ 12% የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 80% ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ሲታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 96% ደርሷል፡፡
  - የፍሳሽ ማጣሪያ (Faecal sludge treatment) ግንባታ የኮንትራክተር ቅጥር ሂደቱን በማስቀጠል ቅጥሩ አሁን ካለበት 77% ወደ100% ማድረስ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 14.95% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 92% ደርሷል፡፡
  - **የ3 ከተሞችን (ጋምቤላ፣ አሶሳ፣ ሰመራሎጊያ) የጥናት እና የዲዛይን** ሥራዉን አሁን ካለበት 70% ወደ 100% በማድረስ ማጠናቀቅ ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 25% ለማከናወን ታቅዶ 24% የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 96% ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 94% ደርሷል፡፡ አማካሪዉ ዝርዝር ጥናት በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡
  - የግንባታ ስራዉን ለማስጀመር የሚያስችል ተቆጣጣሪ አማካሪ ቅጥር ሂደትን ለማስጀመር ቢጋር በማዘጋጀት ቅጥሩ 100% እንዲጠናቀቅ ድጋፍ መስጠት ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 40% ለማከናወን ታቅዶ 29% የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 73% ነዉ፡፡ በአጠቃላይ

ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 29% የደረሰ ሲሆን ቢጋር ተዘጋጅቶ ግምገማ ላይ ይገኛል፡፡

- በ13 ከተሞች (ጅማ፣ ነቀምቴ፣ ሻሸመኔ፣ አሰላ፣ ቢሾፍቱ፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ደ/ብርሃን፣ ጅግጂጋ፣ ደገሀቡር፣ወ/ሶዶ፣አ/ምንጭ፣ እናሐረር) በአማካሪ የሚቀርቡትን የጥናት እና ዲዛይን ስራዎችን ክንዉናቸዉ እንደሚከታለዉ ቀርቧል፣
    - በኦሮሚያ ክልል ስር ለሚገኙ ሶስት ከተሞች (አሰላ፣ቢሾፍቱ እና ሻሸመኔ) የከተማ አቀፍ የሳኒቴሽን ጥናቱን አሁን ካለበት 10% ወደ 100% ለማድረስ በቅንጅት መስራት ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 41% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 51% የደረሰ ሲሆን አማካሪ ድርጅቱ የተሰጠዉን ግብረ መልስ በማካተት የመጨረሻዉን የነባራዊ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡
    - በኦሮሚያ ክልል ስር ለሚገኙ ሁለት ከተሞች (ጅማ እና ነቀምቴ) የከተማ አቀፍ የሳኒቴሽን ጥናቱን አሁን ካለበት 55% ወደ 100% ለማድረስ በቅንጅት መስራት ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 30% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 85% የደረሰ ሲሆን የአዋጭነት ዝርዝር ጥናት ሥራዉ እየተከናወነ ይገኛል፡፡
    - በአማራ ክልል ስር ለሚገኙ ሶስት ከተሞች (ደሴ፣ ጎንደር እና ደብረብርሐን) የከተማ አቀፍ የሳኒቴሽን ጥናቱን አሁን ካለበት 50% ወደ 100% ለማድረስ በቅንጅት መስራት ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 40% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 90% የደረሰ ሲሆን አማካሪ ድርጅቱ ዝርዝር የአዋጪነት ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡
    - በሶማሌ ክልል ስር ለሚገኙ ሁለት ከተሞች (ጅግጅጋ እና ደገሐቡር) የከተማ አቀፍ የሳኒቴሽን ጥናቱን አሁን ካለበት 50% ወደ 100% ለማድረስ በቅንጅት መስራት ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 40% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 90% የደረሰ ሲሆን አማካሪ ድርጅቱ የነባራዊ ጥናት በተሰጠዉ ግብረ መልስ መሰረት በማጠናከር ላይ ይገኛል፡፡

- በደቡብ ክልል ስር ለሚገኙ ሁለት ከተሞች (አርባ ምንጭ እና ወላይታ ሶዶ) የከተማ አቀፍ የሳኒቴሽን ጥናቱን አሁን ካለበት 25% ወደ 100% ለማድረስ በቅንጅት መስራት፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 30% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 55% የደረሰ ሲሆን አማካሪዉ ዝርዝር የአዋጭነት ሥራ በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡
- የሐረር ከተማን የከተማ አቀፍ የሳኒቴሽን ጥናት አሁን ካለበት 85% ወደ 100% ለማድረስ በቅንጅት መስራት ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 15% ለማከናወን ታቅዶ 10% ተከናዉኗል፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ሲታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 95% የደረሰ ሲሆን አማካሪዉ የመጨረሻዉን የጥናት ዉጤት በማጠናከር ላይ ይገኛል፡፡

* በ 8 ከተሞች (ጅማ፤ ባ/ዳር፤ ቢሾፍቱ፤ ጎንደር፤ ሰመራሎጊያ፤ ደገሀቡር፤ ወ/ሶዶ እና አ/ምንጭ) ላይ እየተገነቡ ላሉ 47 የህዝብና 48 የጋራ መፀዳጃ ቤቶች በመስክ በመገኘት ሥራዎቹ በዉለታ መሠረት እየተሠሩ መሆኑን መከታተልና ለከተሞቹ ግብረ መልስ በመስጠት ስራዉን አሁን ካለበት 75% ወደ 100% እንዲደርስእገዛማድረግ ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 12.5% ለማከናወን ታቅዶ 8% የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 64% ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 83% ደርሷል፡፡ አፈጻጸሙ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት የዕቃዎች ዋጋ መናር፤የሁለት ከተሞች(ጅማና ቢሾፍቱ) ዉል በመቋረጡ፤ የተቋራጮች ዝቅተኛ አፈጻጸም(በኮንትራት ጊዜ የተሞላዉ ዋጋ በጣም አነስተኛ መሆን ለምሳሌ ወ/ሶዶ)
* **በቀሩት 9 (አሰላ፤ አዳማ፤ ሐረር፤ አሶሳ፤ ደ/ብርሃን፤ ደሴ፤ ጋምቤላ፤ ድሬደዋ እና (ነቀምቴ) ላይ እየተገነቡ ላሉ 53 የህዝብ እና 51 የጋራ መፀዳጃ** ቤቶች በመስክ በመገኘት ስራዎቹ በውለታው መሰረት እየተሰሩ መሆኑን መከታተልና ለከተሞቹ ግብረ መልስ በመስጠት ስራው አሁን ካለበት 49% ወደ 100% እንዲደርስ እገዛ ማድረግ ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 25.5% ለማከናወን ታቅዶ 13% የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 51% ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ሲታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 62% ደርሷል፡፡ አፈጻጸሙ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት የማጠቃለያ ዕቃዎች (finishing materials) ዋጋ መናር፤የኮንትራት ዉል መቋረጥ (ነቀምቴ)፤ የተቋራጮች ዝቅተኛ አፈጻጸም ( ደ/ብርሃን)፤ በጦርነቱ ምክንያት ሥራዎች መቋረጥ( ደሴ) እንደ ዋነኛ ምክንያት ሆኗል፡፡

- በ7 ከተሞች (ባ/ዳር፣ ሻሸመኔ፣ ጅግጅጋ፣ ሀዋሳ ፣አዳማ፣ ድሬደዋ እና ጎንደር ) ለሚገነቡ አዳዲስ ዘመናዊ 38 የህዝብ እና 58 የጋራ መፀዳጃ ቤቶች የኮንትራክተር ቅጥርን ለማከናወን ሙያዊ እገዛ በማድረግ ወደ ግንባታ እንዲገቡ ማገዝ፡ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 53.33% ለማከናወን ታቅዶ 25% የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 47% ነዉ፡፡ አፈጻጸሙ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት ከተሞቹ ወደ ሥራ ለመግባት የመሬት ዝግጅት በወቅቱ ባለመጨረሱና የጨረታ ሰነድ ዝግጅቱ ጎን ለጎን ባለመከናወኑ እንደ ዋነኛ መዘገየት የታየ ሲሆን ከሰባቱ ከተሞች ባ/ዳርና ሻሸመኔ ከተሞች ይህንን ሂደት አልፈዉ ወደ ግንባታ ገብተዋል፡፡
- ከ Faecal Sludge Treatment Plant Technology እና Faecal Sludge Management ጋር የተያያዙ የቴክኒክ ስልጠናዎችን ለ88 ባለሙያዎች በ1 ዙር የሀገር ውስጥ ሥልጠና በመስጠት በዘርፉ ያለውን የቴክኖሎጂ አማራጮች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስቻል እና የሚገነቡት የፍሳሽ ማጣሪያ መሰረተልማቶችን ዘላቂነት ማረጋገጥ ስራ ለማከናወን ታቅዶ ሥራዉ አልተከናወነም፡፡
- የፕሮጀክቱን አላማ ለማሳካት በኮሚሽኑ ስር ካሉ ዳይሬክቶሬቶች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የክትትልና የማስተባበር ስራ ማከናወን ፡- ከዓመቱ 100% ዕቅድ ዉስጥ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 50% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡
- የውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎቶችን የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች ትግበራ አፈፃፀም እና ክትትል ማድረግ (የሩብ አመት እና ዓመታዊ ሪፓርት ማዘጋጀት) ፡- ከዓመቱ 100% ዕቅድ ዉስጥ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 50% ለማከናወን ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡
- በአጠቃላይ በመጀመሪያው 6 ወራት የ23 ከተሞች የፍሳሽ ማስወገጃ ተቋማት ፕሮጀክት 9.7% ታቅዶ 6.95% የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 71.2% ነዉ፡፡

## 2. ከአይነ ምድር የፀዳ አካባቢ (ODF) ፕሮጀክት

- ለStandard Latrine Design and Catalogue ከሚቀጠረው አማካሪ ድርጅት የሚቀርቡ ግብዓቶችን በመገምገም እና ስራውን በመከታተል አሁን ካለበት 55% ወደ 100% እንዲደርስ ማድረግ ፡- በ6 ወራት 45% ለማከናወን ታቅዶ 31.5% (የዕቅዱ 70%) የተከናወነ ሲሆን፣በአጠቃላይ ከዓመቱ ዕቅድ አንጻር ስታይ እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ 86.5% የደረሰ ሲሆን አፈጻጸሙ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት ሚ/ር መ/ቤቱ በአዲሱ መዋቅር መሰረት ተደራጅቶ ባለመጠናቀቁ ከገንዘብ ሚ/ር የሚለቀቀዉ በጀት በመዘገየቱ ሥራዉ በታቀደዉ መሰረት ባለመከናወኑ ነው፡፡

- በዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና ጤና ሚኒስቴር በጋራ እየተዘጋጀ ያለውን PIM (Project Implentation Manual ) አበልፅጎ ለማጠናቀቅ በ6 ወራት 8% ለማከናወን የታቀደ ቢሆንም ሥራዉ በሁለት ሚ/ር መ/ቤቶች የሚከናወን ሆኖ በሁለቱ መ/ቤቶች አለመቀናጀትና በሚ/ር መ/ቤታችን አዲስ አደረጃጀት ምክንያት ሥራዉ አልተከናወነም፡፡
- በዉሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና ጤና ሚኒስቴር ጋር እየተዘጋጀ ያለውን የመግባቢያ ሰነድ (Memorundum Of Understanding ) አበልፅጎ ሙሉ በሙሉ እንዲጠናቀቅ ሙያዊ እገዛ ማድረግ ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ የታቀደ ቢሆንም በሁለቱ መ/ቤቶች አለመቀናጀትና በሚ/ር መ/ቤታችን አዲስ አደረጃጀት ምክንያት ሥራዉ አልተከናወነም፡፡
- ለ6 ከተሞች (ሆሳዕና፤ ባቱ፤ አምቦ፤ ደብረ ማርቆስ፤ ኮምቦልቻ እና ጎዴ) 12-ዘመናዊ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ግንባታን ለማከናወን (BID-Document) ከሚመለከተው ዳይሬክቶሬት ጋር በጋራ በመሆን ማዘጋጀት ፡- እስከ ሁለተኛዉ ሩብ ዓመት 100% ለማከናወን ታቅዶ 60% የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 60% ነዉ፡፡
- በ6 ከተሞች (ሆሳዕና፤ ባቱ፤ አምቦ፤ ደብረ ማርቆስ፤ ኮምቦልቻ እና ጎዴ) ለሚገነቡት 12 ዘመናዊ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች ወደ ግንባታ ከተገባ ቦኃላ በመስክ በመገኘት የግንባታ ቁጥጥር በማከናወን ሙያዊ ግብረ መልስ በመስጠት ግንባታውን 100% የማድረስ ስራ 40% የግንባታ ሥራዉን እና የጨረታ ዝግጅት ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ሥራዉ አልተከናወነም፡፡
- በአጠቃላይ በስድስት ወራት የአይነ ምድር የፀዳ አካባቢ ፕሮጀክት በአማካኝ 5.1% የፊዚካል ስራውን ለማከናወን ታቅዶ 1.61 % የተከናወነ ስሆን አፈጻጸሙ 32% ነዉ፡፡ አፈጻጸሙ አነስተኛ የሆነበት ምክንያት መ/ቤቱ በአዲሱ መዋቅር መሰረት ተደራጅቶ ባለመጠናቀቁ ከገንዘብ ሚ/ር የሚለቀቀዉ በጀት በመዘግየቱ ሥራዉ በታቀደዉ መሰረት አልተከናወነም፡፡

## ሐ በመጠጥ ውሀና ሳኒቴሽን መሠረተ ልማት ዘላቂነት ማረጋገጥ ን/ ፕሮግራም

### የካፒታል ፕሮጀክት

በዚህ ን/ፕሮግራም በበጀት አመቱ አንድ ፕሮጀክት (የፍሎረሲስ መከላከያ ፕሮጀክት) እየተተገበረ ሲሆን የዚህም አፈፃፀም ቀጥሎ ቀርቧል፡-

### 1. የፍሎራይድ መከላከል ፕሮጀክት

- በበጀት አመቱ የፍሎራይድ ፕሮጀክት የ Impact assessment ስራ ከ30% ወደ 100% ለማጠናቀቅ የኮንሰልታንት ቅጥር እንዲከናወን የኮንትራት ስምምነት ሰነድ በመዘጋጀት ሲሆን በ6 ወራት 20% ለማከናወን ታቅዶ 10% (የዕቅዱ 50%) ተከናዉነዋል፡፡

- በደቡብ ክልል በዱግና ፋንጎና ማረቆ ወረዳ ላይ በ2013 በጀት ዓመት የተጀመሩትን 2 የፍተሻ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ከ 80% ወደ 100% ለማከናወን ታቅዶ የሁለቱ ሣይቶች የጉድጓድ ቁፋሮ ሥራ ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል፡፡
- በአሁን ሰዓት በዱግና ፋንጎ ወረዳ ላይ የአማራጭ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ዝርዝር የዲዛይን ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በስድስት ወራት ከታቀደው 15% ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን ፕርጀክቱ እስከ አሁን በአጠቃላይ 95% ደርሷል፡፡
- በደቡብ ኮርያ መንግሰት ድጋፍ ለዱጉዳ ወረዳ በተመረጡ 4 ቀበሌዎች አማራጭ የመጠጥ ዉሃ ግንባታ ላይ ድጋፍ በማድረግ ስራው ከነበረበት 10% ወደ 50% የማድረስ ስራ በ6 ወራት ከታቀደው 11% ውስጥ 9% (የዕቅዱ 82%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም የ1 የፍተሻ ጥልቅ ጉድጓድ ተጠናቋል፡፡ ከዚሁ ጋር ከተመረጡት 3 ቀበሌዎች ማለትም ቆዬ ጀጀባ፣ዋልዳ ሃፋ፣ ሃፋ ቀመላ ፣ቆርኬ አዳማ) የአማራጭ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ዝርዝር የዲዛይን ሥራ በኮንሰልታንት ተሰርቶ ተጠናቋል፡፡ የአማራጭ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ግንባታም ለማስጀመር የውሃ ሥራ ተቋራጭ አሸናፊ ኮንትራክተር ተመርጦ የኮንትራት ውል ስምምነት ተፈርሞ የሲቪል ግንባታ ሥራው በመከናወን ላይ ሲሆን የውሃ መስመር ቧንባዎች ግዢም ተፈፅሟል፡፡
- በበጀት አመቱ በደቡብ ኮሪያ መንግስት ድጋፍ ኦሮሚያ ክልል ቦቶር ጦላይ ወረዳ ከታ ድሬ ከተማ ላይ የፍሎራይድ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ግንባታ ድጋፍ በማድረግ ከ40% ወደ 100% የማጠናቀቅ ስራን በተመለከተ፡- በ6 ወራት 20% ለማከናወን ታቅዶ 56% (የዕቅዱ 280%) የተከናወነ ሲሆን በዚህም ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ እስከ አሁን ያለበት የአፈፃፀም ደረጃ 96% ደርሷል፡፡
- በአፍሪካ ልማት ባንክ ድጋፍ በኦሮሚያ እና ደ/ብ/ብ/ህ/ ክልሎች በ2 ሣይቶች በሪቨርስ ኦስሞሲስ የሚሰራ የፍሎራይድ ቴክኖሎጂ ሽግግር ማጣሪያ ግንባታ የማጠናቀቅ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ በስድስት ወራት ታቅዶ የነበረው የተከላ (Installation Works) ሥራውን ማስጀመር አልተቻለም፡፡
- በCWA ድጋፍ የፍሎራይድ መከላከል የ10 አመት መሪ ስትራቴጂክ ዕቅድ በኮንሰልታንት ለማስጠናት ቢጋር (TOR) የተዘጋጀና ግዢ መፈፀም እንዲቻል በዓለም ባንክ ይሁንታ (No Objection) የተሰጠ ሲሆን በስድስት ወራት 30% ለማከናወን ታቅዶ 10% የተከናወነ ሲሆን

አፈፃፀሙ 33% ነው፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የግዢ አፅዳቂ ኮሚቴ ለማፀደቅ ረዘም ያለ ጊዜ በመዉሰዱ ነው፡፡ በአጠቃላይ ስረው 20% ደርሷል፡፡

- በአጠቃላይ በስድስት ወራት የፕሮጀክቱን የፊዚካል ስራዎች 5% ለማከናወን ታቅዶ 4.14% የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 83%፣

መ. የአቅም ግንባታና ቴክኖሎጂ ልማት ን/ ፕሮግራም

## የካፒታል ፕሮጀክት

- የስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ 1 ሰነድ በዕቅድ ተይዞ በራስ አቅም የተዘጋጀ ሲሆን በገለልተኛ አካል እንዲጠና አስፈላጊ የቢጋር ስራዎች እና 12 ነባርና አዲስ የስልጠና ቢጋር በመከለስና በማሻሻል የማዘጋጀት ስራ 100% ለማከናወን ታቅዶ የእቅዱን 82% ተከናዉኗል፡፡
- ለመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ቴክኖሎጂ መረጣ መመሪያ 1 ሰነድ የማዘጋጀት ስራ 50% ታቅዶ 39% (የዕቅዱ78%) ተከናዉኗል፡፡ በዚህም የቴክኖሎጂ መረጣ ድራፍት ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡
- 5 ሀርድዌርና 10 ሶፍትዌሮች ግዥ አቅርቦትና ተከላ ስራዎችን ትግበራን 40% ለማከናወን ታቅዶ 37% (የዕቅዱ 93%)፣ 3 ለመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሲስቴም ጥናትና ዲዛይን ዕቃዎችንና መሳሪዎችን ግዢ ሂደት 50% ለማከናወን ታቅዶ 47%(የዕቅዱ 94%) እና ለ5 የከተማ ውሃ አገልግሎቶች አነስተኛ የውሃ ጥራት ላቦራቶሪዎችን ማቴሪል በግዥ ማደራጀትና ሥራዎችን መደገፍ 50% ታቅዶ 47% (የዕቅዱ 94%) ተከናዉኗል፡፡
- የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ቴክኖሎጂ ልማት (በሃርድዌር፣ ሶፍትዌር፣ ሰንሴር እና በማኔጅመንት ሲስተም) የጥናትና ምርምር ስራዎችን ከምርምር ተቋማት፣ ቴክኖሎጂ አመንጪዎች/አምራቾች እና ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ ለማካሄድ የመግባቢያ/ ስምምነት ሰነዶችን የማዘጋጀት ስራ 50% ለማከናወን ታቅዶ 44% (የዕቅዱ 88%) ተከናዉኗል፡፡
- የተቀናጀ የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ማኔጅመንት ድጋፍ (በመጠጥ ውሃ አቅርቦት አይነምድር ማስመጠጥ፣ ፍሳሽ ማስወገድና ኢኮሎጂ ሳኒቴሽን) ከዩኒቨርሲቲ/ኢ.ው.ቴ./ ከልቀት ማዕከላት/ እና ቴ.ሙ.ሥ.ኮ. ጋር በጋራ የሚሠሩ የምርምር ሥራዎችን የመደገፍ ተግባር 40% ለማከናወን ታቅዶ 27% (የዕቅዱ 68%) ተከናዉኗል፡፡
- በመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ዘርፍ ከመንግስትና መ.ያ.ድ ጋር የትብብርና ድጋፍ ተሳትፎ ስምምነት የማድረግ ሥራዎች መደገፍ 50% ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ተከናዉኗል፡፡ መ.ያ.ድ ጋር በጋራ ለመስራት የግንዛቤ መድረክ በማዘጋጀት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

- ለአስቸኳይ ድጋፍና ከባድ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችንና ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ለሚያስገቡ 2 ድርጅቶች የማመቻቸትና የመደገፍ ስራ 45% ለማከናወን ታቅዶ 30% (የዕቅዱ 68%) ተከናውኗል፡፡
- የዘርፉን/የሴክቴሩን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ከማሳደግ አንፃር በፌደራልና በክልል ደረጃ ድጋፍ የማድረግ ስራዎችን 50% ለማከናወን ታቅዶ 37% (ዕቅዱ 74%) እና ለመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ሴክተር የአቅም ግንባታ የተፅእኖ ግምገማ፣ የፍላጎት ዳሰሳ እና የአቅም ግንባታ ዕቅድ የማዘጋጀት ስራ 50% ለማከናወን ታቅዶ 39 % (የዕቅዱ 78%) ተከናዉኗል፡፡ በዚህም ከተጽኖ ግምገማ ውጭ የተቀሩት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡
- በአጠቃላይ በፕሮጀክቱ የመጀመሪያ 6 ወራት የፊዚካል ስራዎች 2.4% ለማከናወን ታቅዶ 1.15% (የዕቅዱ 48%) ተከናውኗል፡፡

የፋይናንስ አጠቃቀም ፡-

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት በፕሮግራሙ ለሚተገበሩ የካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 717.944 ሚሊ. እንዲሁም ለመደበኛ ስራዎች ብር 13.74 ሚሊ በጠቅላላው ብር 731.688 ሚሊ ስራ ላይ ለማዋል ታቅዶ በመደበኛ ብር 2.743 ሚሊ. እንዲሁም በካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 263.65 ሚሊ. በድምሩ ብር 266.395 ሚሊ. (የእቅዱን 36%) ስራ ላይ ማዋል የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያትም በየፕሮግራሞቹ ስር ቀርቧል፡፡

## ሠ. የውሃ ልማት የብድር ፈንድ አስተዳደር ን/ፕሮግራም

### ግብ1. የፋይናንስ አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ

- ከተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች ቀደም ሲል ቃል በተገባው መሰረት በግማሽ በጀት ዓመቱ ብር 1.179 ቢሊዮን ለብድር የተፈቀደ በጀት ማሰባሰብና ወደ ጽ/ቤቱ አካውንት ገቢ ለማድረግ ታቅዶ ብር 413.20 ሚሊዮን (35.02%) በማሰባሰብ ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡
- ቀደም ሲል ቃል በተገባው መሰረት የፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን የመዋጮ ገንዘብ (matching fund) ብር 597.52 ሚሊዮን ሰብስቦ ገቢ ለማድረግ ታቅዶ ብር 51.20 ሚሊዮን ከክልሎችና ከተበዳሪ ከተሞች ማሰባሰብ ተችሏል፡፡

### ግብ2. የብድር አቅርቦት አቅም በማሳደግ ከ25.8 ቢለዮን ወደ 35.049 ቢሊዮን ማድረስ

- በሪፖርት ጊዜ ውስጥ ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የሚሆን ብር 0.20 ቢሊዮን የብድር ፈንድ ለማቅረብ ታቅዶ ማከናወን ያልተቻለ ሲሆን ከሚታሰቡት የተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ዘዴዎች መካከል ከባንክ ከሚቀመጠው የሂሳብ ወለድ እና ከብድር ተመላሽ

ከሚሰበሰበው ወለድ ላይ ብር 90 ሚሊ. የወለድ ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር 59.50 ሚሊዮን 66% ማከናወን ተችሏል፡፡

**ግብ3. የብድር ተሰብሳቢ አቅምን በማሳደግ ከ694 ሚለዮን ወደ 2.44 ቢሊዮን ማድረስ**

- የብድር ተሰብሳቢዎችን በወቅቱ በመሰብሰብ በግማሽ በጀት ዓመቱ ውስጥ ብር 108.76 ሚሊዮን ለመሰብሰብ ታቅዶ 81.77 (75.18%) በላይ መሰብሰብ ተችሏል፡፡
- በግማሽ በጀት ዓመቱ 6 ለሚሆኑ ብድር በመመለስ ላይ የሚገኙ እና በቀጣይም መመለስ የሚጀምሩትን የውሃ አገልግሎቶች የመስክ ክትትል በማድረግ ሙያዊ ድጋፍና ምክር የመስጠት ዕቅድና በሪፖርት ጊዜ ውስጥ ቀደም ብሎ በተጠናቀቁና ብድር መመለስ የጀመሩ 15 የውሃ አገልግሎቶችን የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ አልተከናወነም፡፡

**ግብ4. የፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን የማስፈፀም አቅም ማሳደግ**

- በሪፖርት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊዉን የሙያ ድጋፍና ይሁንታ በመስጠት 1 የአማካሪ ድርጅቶች ቅጥር እንዲከናወን ለማድረግ ታቅዶ 2 እንዲሁም የ6 ከተሞችን የሳኒቴሽን ፕሮጀክቶች የአማካሪ ድርጅት ቅጥር በማከናወን የጥናት ስራዉ እንዲጀመር ለማድረግ ታቅዶ የአማካሪ ቅጥሩን ማከናወን ተችሏል፡፡
- በሪፖርት ጊዜ ውስጥ የጥናትና ዲዛይን ስራዎች የሚሰራላቸው የ6 ከተሞችን አማካሪዎች በወቅቱ እንዲጠናቀቁ የክትትል ስራ ለማከናወን ታቅዶ የ3ቱንም (50%)፤ በግማሽ በጀት ዓመቱ 15 የሚደርሱ የግንባታና ተዛማጅ ስራ /CI7VIL Work/ ተቋራጭ ቅጥር እንዲፈጸም ሙያዊ ድጋፍና ይሁንታ ለመሰጠት ታቅዶ 14 (93%)፤ በሪፖርት ጊዜ ውስጥ በግንባታ ላይ ለሚገኙና 14 ለሚሆኑ ፕሮጀክቶች ለአስፈጻሚዎቻቸው አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በአማካኝ 53.54 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15.86 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡
- በሪፖርት ጊዜ ውስጥ በግንባታ ላይ ለሚገኙና 10 ለሚሆኑ ፕሮጀክቶች ለአስፈጻሚዎቻቸው አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በአማካኝ 19.04 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 15.61 በመቶ ማከናወን የተቻለ ሲሆን በግንባታ ላይ ለሚገኙና 20 ለሚሆኑ ፕሮጀክቶች ለአስፈጻሚዎቻቸው አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በአማካኝ 6.70 በመቶ ለማከናወን ታቅዶ 2.05 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

**ግብ5. የመረጃ አያያዝና አደረጃጀትና ልውውጥ ስርዓትን ማጎልበት**

- በሪፖርት ጊዜው ውስጥ በጽ/ቤቱ ደረጃዉን የጠበቀና ዘመናዊ የዳታ ማዕከል ለማቋቋም /ለመገንባት/ ለሚያስፈልጉ ስራዎችን ለሚያጠና አማካሪ ቅጥር የሚሆን /ToR/ ለማዘጋጀት ታቅዶ 22 በመቶ የሚሆነውን የቅድመ ዝግጅት ስራ ማከናወን ተችሏል።

**የበጀት አጠቃቀም**

**የመደበኛ በጀት አፈጻጸም**

- በሪፖርቱ ጊዜዉ ዉስጥ ሰብአዊ ለሆኑ አገልግሎቶች/ለደመወዝና ተዛማጅ ወጪዎች/ በጀት ታቅዶ ከነበረዉ 2.733 ሚ.ሊ ብር ዉስጥ ብር 1.780 ሚ.ሊ. በማከናወን ከዕቅዱ 65% ተከናዉኗል:: ለሥራ ማስኬጃ (ሰብአዊ ላልሆኑ ወጪዎች) በግማሽ ዓመቱ ታቅዶ ከነበረዉ 5.988 ሚ.ሊ. ብር ውስጥ ፣ 1.545 ሚ.ሊ. ብር ወጪ በማድረግ ከዕቅዱ 25.80% ተከናውኗል፡፡ በጥቅሉ በግማሽ ዓመቱ ታቅዶ ከነበረው ብር 8.722 ሚ.ሊ. ውስጥ ብር 3.326 ሚ.ሊ. /38%/ ብቻ በሥራ ላይ ውሏል፡፡

## 1.5. ፕሮግራም አራት፡ የኢነርጂ ልማትና አስተዳደር

የኢነርጂ ዘርፉ የተሻሻሉና ወጪ ቆጣቢ፣ ከከባቢ አየር ብክለት ጽዱ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ ምንጮችን ጥናት በማካሄድ ፣ አዳዲስ ዲዛይኖችን በማላመድ፣ በማሸጋገርና በማስፋፋት፣ ኀይል የማመንጨት አቅምን በማሳደግ፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነትን በማረጋገጥ፣ የሃይደሮ ፓዎር ልማትን በማስፋፋት ለማህበረሰብ ስራን በቀላሉ ለማከናወን የሚያስችል የኢነርጂ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ስርጭት እንዲኖር ጥረት እያደረገ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡

### 1.5.1 የሃይድሮፓወር ጥናትና ዲዛይን ንኡስ ፕሮግራም

**ሀ/ የዳቡስ ሃይድሮፓዋር የአዋጭነት ጥናት**

- በ2014 በጀት አመት ለፕሮጀክቱ የፊዚቢሊቲ ጥናት ለ2ኛዉ ሩብ ዓመት ከተያዘውን አጠቃላይ ክብደት (7%) ውስጥ እስከ 2ኛዉ ሩብ ዓመት መጨረሻ (7%) ፐርሰንት ለማከናወን ታቅዶ ሳይከናወን ቀርቷል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የጂኦቴክኒካል ጥናት ኮንትራክተር ለመቅጠር እየተካሄደ ባለው የኮንትራት ድርድር ላይ ባጋጠመው ያልተጠበቀ መጓተት ነው፡፡ ባለዉ ወቅታዊ ሁኔታ እና የዋጋ መናር ምክንያት አማካሪው ድርጅት ለጥናት ሥራው ፍላጎት አለመኖሩን አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የፕሮጀክቱ የእስከ አሁን አፈጻጸም የቅድመ ዝርዝር (የፕሪፊዚቢሊቲ) ጥናቱን 35% ና የፊዚቢሊቲ ጥናቱን 40% በማጠናቀቅ አጠቃላይ አፈጻጸሙ 75% ላይ ነው ያለው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በድርድር ላይ ያለዉ ኮንትራክተር የዋጋ ልዩነት ስለሚኖር በሚል ድርድሩን እያጓተተ ይገኛል፡፡

ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር
MINISTRY OF WATER AND ENERGY

ለ/ የስምጥ ሸለቆ (RV-3) የቅድመ -አዋጭነት ጥናት

- የስምጥ ሸለቆ (RV-3) ጥናት በ2012 የበጀት ዓመት የተጀመረ የቅድመ ዝርዝርና የዝርዝር ጥናት ፕሮጀክት ነው፡፡ በዚሁ በጀት ዓመት የፕሮጀክቱን አዋጭነት ጥናት ለማካሄድ የሚችል አማካሪ ድርጅት ለመቅጠር እየተካሄደ በነበረው የፕሮጀክቱ የጨረታ ሂደት ጥናቱን ለማካሄድ በቀረበዉ የጨረታ ሰነድ ላይ ጨረታ አጽዳቂ ኮሚቴ ይኹንታ ለመስጠት በማጓተቱ ጨረታ አዉጥቶ አማካሪ መቅጠር አልተቻለም፡፡

### 1.1. የኢነርጂ ጥናትና ምርምር ንዑስ ፕሮግራም

- የፈሳሽ ነዳጅን ወደ ጋዝ ነዳጅ ለመቀየር የሚያስችል የጥናት ሰነድ እየተዘጋጀ ሲሆን አፈጻጸሙም 30 ፐረሰንት ደርሷል
- የባዮፊዩል ማምረቻና መገልገያ መሳሪያዎችን ለማሻሻል የሚረዳ አንድ የጥናት ሰነድ እየተዘጋጀ ሲሆን ዝግጅቱም 25 ፐርሰንት ደርሷል

### 1.2. የኢነርጂ ልማትና ሽግግር ንዑስ ፕሮግራም

- አዲስ የኢታኖል ምድጃ ቴክኖሎጂ ዲዛይን በመስራት ለምርት ማዘጋጀት ስራ እየተከናወነ ይገኛል አፈጻጸሙም 85 ፐረሰንት የደረሰ ሲሆን 24 ልዩ ልዩ የኢነርጂ ቴክኖሎጂ ናሙናዎች ለማምረት ታቅዶ 22 ተከናውኗል አፈጻጸሙም 91.7% ደርሷል፡፡
- 60 የኢነርጂ ቴክኖሎጂ እና ምንጮችን ለመፈተሽ ታቅዶ 97 ተከናውኗል ፡፡ አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ሲሆን የተጠናቀቀ የባዮጋዝ እንጀራ መጋገሪያ ምድጃ ለማውጣት ታቅዶ በጀት ባለመለቀቁ ምክንያት አልተከናወነም
- 2 በፀሐይ ሀይል የሚሰራ የምግብ ማብሰያ ቴክኖሎጂዎችን ማላመድ ታቅዶ 2፣ አንድ የፀሐይ ማድረቂያ ቴክኖሎጂ ማላመድ ስራ እየተከናወነ መሆኑና 500,000 የሚሆኑ ምድጃዎችን ለማሰራጨት ታቅዶ 455,000 ምድጃዎች ተሰራጭተዋል አፈጻጸሙም 91% ነው
- በመስክ የማብሰያ ምድጃ ቴክኖሎጂ በፍተሻ ደረጃ እንዲወጣ በማድረግ ማጸደቅ በደረጃ አጽዳቂ ካውንስል አለመሰብሰብ ምክንያት ቶሎ ማጠናቀቅ ያለመቻሉና የማብሰያ ምድጃ ቴክኖሎጂዎች ከገበያ እና አምራቾች ናሙና በመውሰድ የብቃት ደረጃቸው ላይ ፍተሻ ማካሄድ ታቅዶ 90% ደርሷል ፡፡
- ለ30 ሰዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ22 ሰዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም 73.3%፣ በዘርፉ ለ500 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ460 ሰዎች የስራ እድል ተፈጥሯል አፈጻጸሙም 92% መድረሱና 55,000 የሚደርስ የጸሃይ ሃይል

ቴክኖሎጂ ስርጭት መረጃ መሰብሰብ ታቅዶ 61,000 መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል አፈጻጸሙም ከ100% በላይ ነው ፡፡

## የካፒታል ፕሮጀክቶች

### ብሄራዊ የባዮ ጋዝ ፕሮግራም

- አዳዲስ 2600 የባዮጋዝ ዳይጀስተሮችን ለመገንባት ታቅዶ 1075 ዳይጀስተሮች የተገነቡ ሲሆን አፈጻጸሙም 41%፣ ለ13000 ለሚሆኑ የገጠር ማህበረሰቦች የባዮ ጋዝ ኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግ ታስቦ ለ5175 ማህበረሰቦች ብቻ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል አፈጻጸሙም 40%፣ ለ2600 የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የባዮ ጋዝ ተረፈ ምርት (bio-slurry) አጠቃቀም ስልጠና መስጠት ታቅዶ ለ1035 ተጠቃሚዎች ብቻ የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙም 40% እንዲሁም ለ5200 የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች የጥገናና የአጠቃቀም ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ2070 ሰዎች ስልጠና መስጠት ተችሏል ፡፡ አፈጻጸሙም 40% ነው፡፡
- ለ1458 ወጣቶችና ሴቶች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ በባዮጋዝ ቴክኖሎጂዎች ግንባታ እንዲሁም ጥገና በሚያካሂዱበት ጊዜ ለ1222 ዜጎች ጊዜያዊ የስራ እድል ተፈጥሯል ፡፡ አፈጻጸሙም 40% ነው፡፡አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በጸጥታ ችግር፣የግንባታ እቃዎች ዋጋ መናርና የባላድርሻ አካላት የበላቤትነት ስሜት አነስተኛ መሆን ናቸዉ፡፡

### ኢትዮ ቻይና ሲሪላንካ የባዮጋዝ፣ ሶላር የሦስትዮሽ ትብብር ፕሮጀክት

- ለሰርቶ ማሳያዎች ለመገንባት የሚያስፈልጉ ስፔሲፊኬሽን ማዘጋጀት በጥቅል 6 የታቀደ ሲሆን 6ቱም ጥቅሎች ተዘጋጅተዋል( 2 ባዮጋዝ ወላይታ ሶዶና ሀረር ፣ 4 ሶላር ወላይታ ሶዶ ሀረርና መርሳ) በተዘጋጀው የእቃዎች ስፔሲፊክ መሰረት የእቃዎችን ግዥ 40% ያህሉን ለማሟላት ታቅዶ 40% ያህሉን ለማከናወን ተችሏል ፡፡
- የሰርቶ ማሳያ ሲስተሞችን መሰረት ያደረገ የምርምርና ስርጸት ማዕከለ በወላይታ ዩኒቨርሲቲ የተቀደ ሲሆን በሲሰተም ዲዛይን ፣ተከላ፣ኦፕሬሽን እና ጥገና ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና ለ15 ሰዎች ለመስጠት ታቅዶ ለ34 ሰዎች ስልጠናውን እንዲወስዱ ተደርጓል ፡፡

### የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፕሮጀክት /RET/

- የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ከገበያና አምራች ናሙና በመውሰድ የጥራት ደረጃቸው ላይ ፍተሻ ማካሄድ ና ድጋፍ ማድረግ፣ በልዩ ልዩ የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች ላይ በተግባር የተደገፈ የመንገድ ላይ የቴክኖሎጂ ትርኢት እንዲካሄድ ድጋፍ ማድረግና ለአራተኛ ዙር

የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራ ውድድር በማካሄድ ስራ ፈጣሪ ወጣቶችን ማበረታታት ተችሏል( ይህም 12 ለመለየት ታስቦ 9(75 %) ተከናውኗል አፈጻጸሙም ዝቅ ያለበት ምክንያት ብቁ ተወዳዳሪ ባለመቅረቡ ነው ፡፡

**ሚኒ -ሃይድሮ የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት**

- ይህ ፕሮጀክት በደቡብ ክልል ሀድያ ዞን የጊቤ ወረዳ ጋሰዳ ቀበሌ የሚገኝ ሲሆን 20 ኪሎ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ለማመንጨት 70 ፐርሰንቱ የተጠናቀቀ ሲሆን ቀሪውን 30 ፐርሰንት(የኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራዎች ክትትልማድረግና የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ማከናወን) ለመጨረስ በእንቀቅስቃሴ ላይ ሲሆን በጀት ባለመለቀቁ ምክንያት ስራው እንዲጓተት ሆኗል ፡፡

**የታዳጊ ክልሎች የማብሰያ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ብቃት ማሻሻያ ፕሮጀክት**

- የፕሮጀክት ሰነድ ፤ ለፕሮጀክቱ አማካሪ ለመቅጠር የአማካሪ ቅጥር ጨረታ ሰነድ ዝግጅትና የፕሮጀክት ትውውቅ ወርክሾ ማካሄድ ተግባራት በዚህ በጀት ዓመት ስድስት ወራት የተካሄዱ ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 1.3. የኢነርጂ መረጃና ቴክኒክ ድጋፍ ንዑስ ፕሮግራም

- የባዮፊዩል ምንጭ፣ ቴክኖሎጂ፣ ተክሎች፣ የገበያና የመሬት መረጃ በመስክ በመሰብሰብ የሪፖርት ሠነድ እየተዘጋጀ የሚገኝ ሲሆን ከመስክ የተሰበሰበ የባዮፊዩል ምንጭ፣ ቴክኖሎጂ፣ ተክሎች፣ የገበያና የመሬት መረጃ በኮምፒዩተር ማስገባትና የሪፖርት ሠነድ እየተዘጋጀ ነው
- ከአሁን በፊት በውጭ አማካሪ የተሰራውን የባዮፊዩል ተክሎች ተስማሚነት (suitability map) ማሻሻያ በማድረግ በመሬት መረጃ ሥርዓት (GIS) የተደገፈ ካርታ የማዘጋጀት ስራ እተከናወነ ሲሆን የባዮፊዩል ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ልማቱ እንዲነቃቃ ሦስት የውይይት ፎረም ማዘጋጀት ታቅዶ በጀት ባለመለቀቁ ምክንያት አልተከናወነም
- በስኳር ፋብሪካዎች 1.6 ሚሊየን ሊትር ኤታኖል እንዲመረት በማስተባበር 1.6 ሚሊየን ሊትር የኢታኖል መጠን ለማብሰያነት እንዲቀርብ ተደርጓል አፈጻጸሙም 100% ነው
- 900 የሚሆኑ ለምግብ ማብሰያነት የሚያገለግል የኤታኖል ምድጃ ለተጠቃሚው ኢንዲደርስ የማስተባበር ስራ የታቀደ ሲሆን 600 (67% ) ለሚሆኑ የኢታኖል ምድጃ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ተደርጓል ፤፤

1.5.2 ንኡስ ፕሮግራም አምስት፡ ብሔራዊ ኤሌክትሪፊኬሽን

**ብሄራዊ ሃይል ማመንጨት አቅም ማሳደግ**

- ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ሃብት የሚሆን 625 ሚሊየን ብር ለማሰባሰብ ታቅዶ 494 ሚሊየን ብር ተሰብስቧል፡፡አፈጻጸሙም 79% ሲሆን ከህዳሴ ግድብ የመጀመርያዉ ዩኒት 375 ሜ.ዋ ለማመንጨት ታቅዶ 375 ሜ.ዋ ማመንጨት ተችሏል አፈጻጸሙ 100% ነው
- የአይሻ ንፋስ ኤሌክትሪክ 80ሜጋዋት የማመንጨት ስራ ማሰጀመር 14.15% ታቅዶ 14.15% ወይም የዕቅዱን 100%፤ የአዳማ 230 ኪሎ ቮልት ሰብእስቴሽን ማከፋፊያ ስራ 17.98% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 17.98% ወይም የዕቅዱን 100% እንዲሁም የሻምቡ 230 ኪሎ ቮልት ሰብእስቴሽን ማከፋፊያ ስራ 26.9% ለማጠናቀቅ ታቅዶ 26.9% ወይም የዕቅዱን 100% ለማከናወን ተችሏል፡፡

**የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ**

- 125000 ከግሪድ ኤሌክትሪክ የማገናኘት ሥራ ታቅዶ 73915 ወይም የዕቅዱን 59% የተከናወነ ሲሆን 4 የሶላር ሚኒ ግሪድ(ሁለት በአማር ክልል፤አንድ በአፋር ክልልና አንድ በትግራይ ክልል) በኤሌክትሪክ የማገናኘት ሥራ ታቅዶ በጸጥታ ችግር ምክንያት አልተከናወነም
- የብሔራዊ ኤሌክትሪፊኬሽ ፕሮግራም አንድ ጊዜ ክትትል እና ግምገማ ለማድረግ ታቅዶ ግምገማዉ የተካሄደ ሲሆን የፕሮግራሙን አፈፃፀም በ3ተኛ ወገን (ሴንትራል ስታትስቲክስ ኤጀንሲ) አንድ ጊዜ ለማስገምገም ታቅዶ ማስገምገም ተችሏል፡፡
- ጂ.አይ.ኤስን (GIS) መሰረት ያደረገ ኤሌክትሪፊኬሽን መረጃ ቋት ማደራጀት ባለሙያ ባለመቀጠሩ ምክንያት እና ለ12 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በኮቪድ 19 ምክንያት አልተካሄደም፡፡
- የህንጻ ግንባታ ዲዛይን የማስፈቀድ ስራና የግዥና ፋይናንስ ኦዲት ምርመራ ማካሄድ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

**የ6 ወራት የፋይናንስ አጠቃቀም**

በዘርፉ በመደበኛ ከተመደበው ብር 5506735 ውስጥ እስከ 6 ወራት መጨረሻ የተመዘገበው አፈፃፀም 3632219 ብር ነው፡፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ ሲሰላ 66% ነው፡፡ እንዲሁም ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተያዘ አጠቃላይ ካፒታልና የድጋፍን በጀት ጨምሮ ዕቅድ 234866900 ብር ሲሆን፣ የተመዘገበው አፈፃፀም 99712964 ብር ነው፡፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ ሲሰላ 42.45% ነው፡፡

## II. የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማት

### 2.1 የኢት/ያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትቲዩት

ዋነኛ ተግባርና ኃላፊነቱ ሀገሪቱን የሚወክል የአየር ሁኔታ መከታተያ ጣቢያ ኔትወርክ በማስፋፋት የሜትዮሮሎጂ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መተንተንና ማከማቸት፣ መረጃዎችን ለመሰብስብ ለማሰራጨት የሚያስችሉ የመገናኛ ዘዴዎችን ማkkም እና አስፈላጊውን የሜትዮሮሎጂ አገልግሎት ለልዩ ልዩ የስራ እንቅስቃሴዎች መስጠትና በዓለም ዓቀፍ ስምምነት መሰረት መረጃዎችን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ መለዋወጥ የሆነው የኢንስትቲዩቱ የ2014 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ቀጥሎ ቀርቧል።

**ግብ** 1: የሀገሪቱን መልክአ ምድር ወካይ የሆነ የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ አውታር በጣቢያ ስርጭት ማስተርፕላን መሰረት በመተግበር የዘመናዊና መደበኛ የጣቢያ ሥርዓት ሽፋንን ከ60% ወደ 64% ማሳደግ፣

- 1ኛ ደረጃ ጣቢያ ማቋቋም በ6 ወሩ 2 ታቅዶ በጣቢያ ማቋቋሚያ ቦታ ችግር ምክንያት ያልተከናወነ ነው።
- 3ኛ ደረጃ ጣቢያ ማቋቋም በ6 ወሩ 2 ታቅዶ፤ የሚቲዎሮሎጂ አጋዥ ቁሳቁሶች (accessories) ማምረት በ6 ወር 36 ለመስራት ታቅዶ 36፤ 50-ትልቅ እና 150-ትንሹ የመሣሪያ ጎጆ በጫረታ ማሰራት በ6 ወር 40% ለማከናወን ታቅዶ 40% እና 100-የሬንጌጅ በጫረታ ማሰመረት በ6 ወር 40% ለማከናወን ታቅዶ 40% ተከናውኗል።

**ግብ** 2: በጥራት፣ በበቂ የቦታና የጊዜ ሽፋን ወቅታዊነታቸውን ጠብቀው የተደራጁና ለተለያዩ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዘርፎች ጥቅም ላይ የሚውሉ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች አቅርቦት አገልግሎትን ከ60% ወደ 64% ማሳደግ፣

- ከክልል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት የተላኩ 13,200 ጥሬ የወረቀት መረጃዎችን ተረክቦ የጥራት ቁጥጥር በማካሔድ በዘመናዊ ዘዴ ማደራጀት በ6 ወር በቁጥር 6,600

ለማከናወን ታቅዶ 6,709፤ የNDVI ስዕላዊ መረጃዎችን በየ 10 ቀናት መጨረሻ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች ማከማቸት፣ ከትንተናው ጋር አያይዞ ማቅረብ እና በድረገጽ ላይ መጫን በ6 ወር በቁጥር 18 ለማከናወን ታቅዶ 18 እንዲሁም የ10 ቀናት የዝናብ መረጃ በማጠናቀር እና በማዘጋጀት ከሳተላይት መረጃ ጋር ማዳቀልና ተንትኖ (Griding and merging) በMap Room ማሰራጨት በ6 ወር በቁጥር 18 ለማከናወን ታቅዶ 18 ተከናውኗል፡፡

- ከሳይኖፕቲክ ጣቢያዎች በየዕለቱ ለተሰበሰቡ መረጃዎች የአስር ቀናት አማካኝ ከፍተኛና ዝቅተኛ የአየር ሙቀት አጠቃላይ የዝናብ መጠን ኬንያ ለሚገኘው ICPAC ማስተላለፍ በ6 ወር በቁጥር 18 ለማከናወን ታቅዶ 18 የተከናወነ ሲሆን የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በማኑዋል መሠረት ከአ.አ ኦብዘርቫቶሪ በቀን 4 ጊዜ መሰብሰብ እና ወደ ኮምፒዩተር ማስገባት በ6 ወር 740 ለማከናወን ታቅዶ 740 ተከናውኗል።

**ግብ 3 የሚቲዎሮሎጂ ጥናትና ምርምር ፕሮግራሞችን ቀርጾ በማካሄድ እና የምርምር አማራጮችን በማስፋት የተሻሻሉና አዳዲስ አሠራሮችን መተግበር፣ የዕውቀት ክፍተትን መሙላት፣ እንዲሁም የአየር ጥራት ምልከታና ትንተና ማካሄድ፤ የምርምር ውጤታማነትን ከ60% ወደ 62% ማሳደግ**

- የኤጀንሲውን ባለሞያዎች በማስተባበር ጥናትና ምርምር ማካሄድ (6 research and studies) በ6 ወር 45 ለማከናወን ታቅዶ 25፤ Joint Scientific Journal of NMA and EtMS ማዘጋጀት እና ማሳተም በ6 ወር 60 ለማከናወን ታቅዶ 20፤ Validation of the ENACT to Station Data over Ethiopia ጥናት ማጠናቀቀቅ በ6 ወር 40 ለማከናወን ታቅዶ 40 እንዲሁም Future Climate Change Projection of Ethiopia Using RegCM3.7 ጥናት ማጠናቀቅ በ6 ወር 60 ለማከናወን ታቅዶ 30 ተከናውኗል
- የአየር ጥራት ቁጥጥር ጣቢያዎች እና መሰረታዊ የአየር ብክለት ሁኔታዎች ትንተና/ Situational Analysis of Air Quality Monitoring Stations and Basic Air Pollutants over Ethiopia ጥናት ማጠናቀቅ በ6 ወር 47 ለማከናወን ታቅዶ 47 ተከናወነ ሲሆን Assessing and Reporting Climate Resilient Green Economy Related Tasks of NMA በ6 ወር 6 ለማከናወን ታቅዶ 6 ተከናውኗል። አፈፃፀሙ 100% ነው።

**የካፒታል ፕሮጀክቶች ዕቅድ አፈፃፀም**

**የሚቲዎሮሎጂ መረጃ አቅርቦት አቅም ማጠናከሪያ ፕሮጀክት**

- 6 ሶስተኛ ደረጃ ጣቢያ ማቋቋም በ6 ወር 2 እና ከ120 ዓመት በላይ የተከማቹ የወረቀት መረጃን ዲጂታይዝ ማድረግ 2ኛ ሩብ አመት ድረስ 710,684 ገፅ መረጃዎች በቁጥር የተለዩ

ሲሆን የተንቀሳቃሽ ስልክ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት 100 ፐርሰንት መዘርጋት በ6 ወር 100% ለማከናወን ታቅዶ 73% ተከናውኗል። አፈፃፀሙ 93% ነው።

**የአቪዬሽን ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዘመኛ ፕሮጀክት ዕቅድ አፈፃፀም**

- ለባሌ ሮቤና እና ጎዴ የሀገር ውስጥ አውሮፕላን ማረፊያዎች ለሚተከሉ የሰው አልባ አየር ሁኔታ መከታተያ ሲስተሞች ግዥና ተከላ ሥራን ማስተባበር በ6 ወር 45% ለማከናወን ታቅዶ 45% የተከናወነ ሲሆን የጥራት ስራ አመራር ሥርዓት ISO 9001:2015 ወሰንን በማስፋት ወደ ሶስቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያዎች ተግባራዊ ማድረግ በ6 ወር 60% ለማከናወን ታቅዶ 60% ተከናውኗል። አፈፃፀሙ 100% ነው።

**የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ተደራሽነትና አጠቃቀም ማሳደጊያ ፕሮጀክት**

- softaware packages ማሟላት እና ማሰልጠን በ6 ወር 2 ለማከናወን ታቅዶ የካፒታል በጀት ባለመለቀቁ ምክንያት ያልተከናወነ ሲሆን በዚህ ፕሮጀክት የሰው ኃይል እውቀትና ክህሎትን በማሳደግ ዙሪያ በሀገር ውስጥ አሰልጣኝ ለ520 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

**የጠረፍ ሚቲዎሮሎጂ ማዕከላት አቅም ማጎልበቻ ፕሮጀክት**

- ለ 3 አብይ ጣቢያዎች ቢሮ መገንባት በ6 ወር 50% ለማከናወን ታቅዶ 30% ተከናውኗል። አፈፃፀሙ 60%፣ ለ7 አብይ ጣቢያ አጥር ግንባታ ማከናወን በ6 ወር 30% ለማከናወን ታቅዶ 20% እንዲሁም ከሜርኩሪ ነፃ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ መሣሪያዎች ግዥ ማከናወን በ6 ወር 70% ለማከናወን ታቅዶ 40% ተከናውኗል።

**የደብረብርሀን ራዳር ጣቢያ ተከላ እና ወደ ስራ ማስገባት ፕሮጀክት**

- ራዳሩ በቫይዛላ መፈብረክ (ማምረት) በ6 ወር 100% ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት የተከናወነ ሲሆን ራዳሩን ከቫይዛላ ወደ ኢትዮጵያ መላክ በ6 ወር 75% ተከናውኗል።
- ራዳሩን የጉምሩክ ፕሮሰስ ጨርሶ ወደ ራዳር መትከያ ጣቢያ/ቦታ ማድረስና የራዳር መትከያ ጣቢያውን ለራዳር ተከላ ማዘጋጀት/የሲቪል ስራውን ሰርቶ ማጠናቀቅ በ6 ወር አልታቀደም።

**የሀዋሳ ራዳር ጣቢያ መትከል**

- ራዳሩ በቫይዛላ መፈብረክ (ማምረት) በ6 ወር 30% ታቅዶ የተከናወነ ሲሆን ራዳሩ በቫይዛላ ወደ ኢትዮጵያ መላክ፣ ራዳሩን የጉምሩክ ፕሮሰስ ጨርሶ ወደ ራዳር መትከያ ጣቢያ/ቦታ ማድረስ እና የራዳር መትከያ ጣቢያውን ለራዳር ተከላ ማዘጋጀት/የሲቪል ስራውን ሰርቶ ማጠናቀቅ በ6 ወር አልታቀደም።

**ሶላር ፓናል ማምረት**

- ሶላር ፓናሉንና ተያያዥ ቁሳቁሶችን በቫይዛላ መፈብረክ/ማምረት በ6 ወር 90% ለማከናወን ታቅዶ 90% እንዲሁም ሶላር ሲስተሙን ወደ ኢትዮጵያ መላክ በ6 ወር 90% ለማከናወን ታቅዶ አልተላከም።
- ሶላር ሲስተሙን የጉምሩክ ፕሮሰስ ጨርሶ ወደ ሻሁራ የራዳር ጣቢያ ማድረስና የሻሁራ ራዳር ጣቢያን ለሶላር ፓናል ተከላ ማዘጋጀት/ሲቪል ስራውን ሰርቶ ማጠናቀቅ በ6 ወር 90% ለማከናወን ታቅዶ አልተከናወነም።

**የአራት የመብረቅ መከታተያ ጣቢያዎች ተከላ**

- የመብረቅ መከታተያ መሳሪያዎች በቫይዛላ ማምረት በ6 ወር 60% ለማከናወን ታቅዶ 60% የተከናወነ ሲሆን የመብረቅ መከታተያ መሳሪያዎቹን የጉምሩክ ፕሮሰስ ጨርሶ ወደ አራቱ ጣቢያዎች መላክ በ6 ወር አልታቀደም።

**የአየር ጥራት መከታተያ ጣቢያ መትከል**

- የአየር ጥራት መከታተያ መሳሪያዎችን በቫይዛላ ማምረት በ6 ወር 30% ለማከናወን ታቅዶ 30% ሲሆን የአየር ጥራት መከታተያ መሳሪየዎቹን ወደ ኢትዮጵያ መላክ በ6 ወር 30% ለማከናወን ታቅዶ 30% ተከናውኗል፤
- የአየር ጥራት መከታተያ መሳሪያዎቹን የጉምሩክ ፕሮሰስ ጨርሶ ማውጣትና የአየር ጥራት መከታተያ ጣቢየዎቹን መትከል እና ወደ ስራ ማስገባት በ6 ወር አልታቀደም።

**የኔትወርክ ዳታ ማኔጅመንት ሲስተም እና ማዕከላዊ የመቆጣጠሪያ ጣቢያ**

- IRIS ሲስተም ማምረት በ6 ወር 30% ለማከናወን ታቅዶ 30% ሲሆን IRIS ሲስተም ወደ ኢትዮጲያ መላክ፤ IRIS ሲስተም የጉምሩክ ፕሮሰስ ጨርሶ ማውጣት እና IRIS ሲስተም መትከል እና ወደ ስራ ማስገባት በ6 ወር አልታቀደም።

**TLP ሲስተም ለመብረቅ መከታተያ**

- TLP ሲስተም ማምረት በ6 ወር 90% ለማከናወን ታቅዶ 90% የተከናወነ ሲሆን TLP ሲስተም ወደ ኢትዮጵያ መላክ፤ TLP ሲስተሙን የጉምሩክ ፕሮሰስ ጨርሶ ማውጣትና TLP ሲስተምን መትከል እና ወደ ስራ ማስገባት በ6 ወር አልታቀደም።

**የሚቲዎሮሎጂ ፎርካስቲንግ ሲስተም ማምረት እና መዘርጋት**

- የሚቲዎሮሎጂ ፎርካስቲንግ ሲስተም ማምረት በ6 ወር 90% ለማከናወን ታቅዶ 90% ተከናውኗል። አፈፃፀሙ 100% ነው።

**የ6 ወራት የፋይናንስ አጠቃቀም**

ኤጀንሲው በመደበኛ ከተመደበው ብር 115,000,000 ውስጥ እስከ በ6 ወራት 57.5 ሚሊየን ለመጠቀም ታቅዶ ብር 55.63 ሚሊዮን በሥራ ላይ ውሏል። አፈፃፀሙም 97% ነው። በካፒታል ከተመደበው በጀት ብር 100,000,000 ውስጥ እስከ በ6 ወራት ብር 50.00 ሚሊየን ለመጠቀም ታቅዶ ብር 23.64 ሚሊዮን በሥራ ላይ ውሏል። አፈፃፀሙም 48% ነው። በአጠቃላይ በአመት ከታቀደው 215,000,000 በጀት በ6 ወር 107.5 ሚሊየን ለመጠቀም ታቅዶ 79.27 ሚሊዮን ብር በሥራ ላይ ውሏል። አፈፃፀሙም 74% ነው። አጠቃላይ የፋይናንስ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት የካፒታል በጀት በወቅቱ ባለመለቀቁና ስራ ላይ ባለመዋሉ ነው።

## 2.2 የኢትዮጵያ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በዋነኝነት ዓላማው ለዘርፉ ባለሙያዎች አጫጭር ተግባር-ተኮር ስልጠናዎችን መስጠትና በቴክኒካል የመደገፍ እና የብቃት ምዘና ማዕከል አገልግሎት መስጠት እንዲሁም ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ ማሸጋገር፣ ጥናት እና ምርምር ማካሄድ እና ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪን የማደራጀትና ዓለም አቀፍ ዕውቅና እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት የ2014 በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ከዚህ በታች ለማቅረብ ተሞክ[ል:-

**አጫጭር ተግባር-ተኮር ስልጠና አፈፃፀም**

- ለ772 የዘርፉ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ በአራት የስልጠና መስኮች፡-
    - በውሃ ሀብት ልማትና ቁፋሮ ቴክኖሎጂ 172 ሰልጣኞች፣
    - በኤሌክትሮ-ሜካኒካልና የቁፋሮ መሳሪያዎች ጥገና ቴክኖሎጂ 90 ሰልጣኞች፣
    - በመጠጥ ውሃ ሳኒቴሽን ምህንድስና ቴክኖሎጂ 142 ሰልጣኞች፣
    - በመስኖና ድሬኔጅ ምህንድስና ቴክኖሎጂ 73 ሰልጣኞች፣
    - ታዳሽ ኃይል ልማት ቴክኖሎጂ ዲፓርትመንት 22 ሰልጣኞች፣

በድምሩ ለ499 (ወንድ 413፣ ሴት 86) 65% የዘርፉ ባለሙያዎች በ5 የስልጠና ዘርፍ እና በ24 የዘርፉ የስልጠና ኮርሶች አጫጭር ተግባር-ተኮር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

**ለቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት የተሰጠ ቴክኒካል ድጋፍ**

- በዚህ 6 ወራት ለ150 የቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት አሰልጣኞችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ፡-

- ○ በሙያ ደረጃ አዘገጃጀት ለ24 (ወንድ) ቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት አሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ስልጠና፣ ካሪኩለም አዘገጃጀት ላይ ለ15 (ወንድ 14 ሴት 1) ኮሌጅ አሰልጣኞች ባለሙያዎች ሥልጠና እና የኢንተርንፕሪነርሽፕ ማስተማሪያ ሞጁል አዘገጃጀት ላይ ለ7 (ወንድ) የኮሌጅ አሰልጣኞች እና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፣
- ○ በውሃ አቅርቦት፣ በኤሌክትሮ-ሜካኒካል እና በመስኖና ድሬነጅ ሙያዎች በTTLM አዘገጃጀት ላይ ለ18 (ወንድ 15 ሴት 3) አሰልጣኞች የሥልጠና ቴክኒካል ድጋፍ እንዲሁም በጥናትና ምርምር ሥነ-ዘዴ እና በፕሮጀክት ፕሮፖዛል አዘገጃጀት ላይ በደቡብ ክልልና በሲዳማ ክልል ከሚገኙ በውሃ ዘርፍ ስልጠና ከሚሰጡ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ለተወጣጡ ለ25 (ወንድ 23 ሴት 2) አመራሮች በወልቂጤ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ተሰጥቷል፣
- ○ በትብብር ሥልጠና አተገባበር ላይ በደቡብ ክልልና በሲዳማ ክልል ከሚገኙ በውሃ ዘርፍ ስልጠና ከሚሰጡ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ለተወጣጡ ለ25 (ወንድ 23 ሴት 2) አመራሮችና አሰልጣኞች በወልቂጤ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ተሰጥቷል፣
- ○ የእሴት ሰንሰለት ሥልጠና ለ27 (ወንድ) አሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ተሰጥቷል፣-

በአጠቃላይ በውሃው ዘርፍ ሙያዎች ስልጠና ለሚሰጡ የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት ለ141 (133 ወንድ፣ 8 ሴት) 94% አሰልጣኞች የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ አፈፃፀሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የአቅም ግንባታ ቴክኒካል ድጋፍ ያገኙ ባለሙዎች በቁጥር በ40 ብልጫ አለው፡፡

## ቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ፡-

- በምስራቅ ሸዋ ዞን ደንካካ ቀበሌ 300 የአካባቢ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገ ስድስት ወጪ ቆጣቢ የውሃ ጉርጓዶችን በመቆፈርና አራት አይነት የውሃ ፓምፖችን (ሶላር፣ አክሰስ፣ ሮፕ እና ኤማስ) ለህብረተሰቡ በማስተላፍ የህብረተሰቡን የውሀ አቅርቦት ችግር መፍታት የተቻለ ሲሆን የሶላር ሀይልን በመጠቀም አማካይ በሆኑ ቦታዎች ህብረተሰቡ የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ተችሏል፣
- የአካባቢው ህብረተሰብ ከብቶች ውሃ የማግኘት ችግርን ለመፍታት የውሃ ገንዳ በመስራት በሶላር ፓምፕ ውሃ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ

የሚተገበረውን የዝናብ ውሃን በስበት ሀይል፤ የተለያዩ ፓምፖችን የመጠቀም ዘዴ ዲዛይን ተዘጋጅቶ የፓይለት ሙከራ በኢንስቲትዩቱ ግቢ ለመትከል እየተሰራ ይገኛል፡፡

**ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ አገልግሎት ተግባራት አፈፃፀም**

- በበጀት አመቱ 75 ናሙናዎች ላይ በተለያዩ ፓራሜትሮች ላይ ለሚካሄደው ፍተሻ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንዲያውቁት ስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ የሚሰጣቸው አገልግሎቶችን የማስተዋወቅና ፍላጎታቸውን የመቀበል ስራ፣ በአራት ክልሎችና በሁለት የከተማ አስተዳደር መጠጥ ውሃ ላቦራቶሪዎች ፍላጎታቸውን የመለየት እና ተቋሙ የሚሰጣቸውን የላቦራቶሪ አገልግሎቶች የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቶ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል፡፡ ከተያዘው ዕቅድ አንፃር አፈፃፀሙ 100% ነው፣
- ሁለት የላቦራቶሪ ኦፔሬሽናል ማኑዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ አንድ የፊዚኮ-ኬሚካል እና አንድ የማይክሮ-ባዮሎጂ ኦፔሬሽናል ማኑዋሎች (100%) ተዘጋጅተዋል በተጨማሪም አምስት የላቦራቶሪ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ አራት (80%) ባለሙያዎች ስልጠናውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፣

2.1.1 የፕሮጀክቶች አፈፃፀም

**በመንግስት የሚሰሩ ፕሮጀክቶች**

**ሀ. የስፔሻላይዝድ ላቦራቶሪ ህንጻ ግንባታ፡-**

- የግንባታው ፊዚካል ሥራ ዕቅድ 100% ሲሆን፣ አጠቃላይ ፊዚካል ክንውኑ ከመጀመሪያው ዕቅድ አንፃር 99.39% ሲሆን፣ በአማካሪ ድርጅት የግንባታ ዲዛይን ለውጥ ምክንያት ተጨማሪ ሥራ ከተሰጠው ጋር ሲነፃፀር አጠቃላይ የፊዚካል ሥራው አፈፃፀም 87% ነው፣

**ለ. የማስተማሪያና የስልጠና ፋሲሊቲዎች ግንባታ**

- የመማሪያ ክፍሎች ዕድሳት (Class Room Renovation) ግንባታ ቴኒስ ሜዳ ፊዚካል ሥራ 100% ለማጠናቀቅ ታቅዶ አጠቃላይ ፊዚካል አፈፃፀሙ 75% ላይ ይገኛል፡፡ የአፈፃፀም ማነስ የታየበት ምክንያት ኮንትራክተሩ በግል ችግር ሥራውን አቋርጦ ስለነበረና በቅርብ ሥራውን በመጀመሩ ነው፡፡
- የግቢው አጥር ግንባታ በወጣው ግልፅ ጨረታ መሰረት በአሸናፊ ሥራ ተቋራጭ ግንባታው እየተከናወነ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም 20 ፐርሰንት ላይ ይገኛል፡፡

## በዕርዳታ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች

### በሞሮኮ ንጉስ መሀመድ 6ኛ የዘላቂ ልማት ፋውንዴሽን የሚገነባው የስልጠና ፋሲሊቲ ህንፃ ግንባታ፡-

- አንድ ህንፃ G+1 (ለቢሮ አገልግሎት፣ ለመማሪያ ክፍሎች፣ ለስብሰባ አደራሽ፣ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ) አገልግሎት የሚውሉ ክፍሎች፣ ሶስት ዎርክ-ሾፖች (Water and waste water treatment, Irrigation system, Electricity, Electromechanical and Renewable energies)፤ ሁለት ላቦራቶሪዎች (Water Physico-Chemical, Microbiological) እና ማስተማሪያ ፋርም (open field, Greenhouse, and Shade house) ጠቅላላ 2,640 ሜ2 ላይ ያረፈ ግንባታ በኮቪድ ምክንያት የዘገየ ቢሆንም፣ አጠቃላይ የፊዚካል ሥራ አፈፃፀም 100% ላይ ነው፣

### በጃይካ የሚደገፍ training operation and management ፕሮጀክት

- E-learning ስልጠና መስጠት የሚያስችል የ 5 TTLM ዝግጅት ላይ ለባለሙያዎቻችን የሥራ ላይ አቅም ግንባታ ሥራ ተከናውኖዋል እንዲሁም ለ12 የኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ እና መካከለኛ አመራሮች መሠረታዊ የአመራር ዕውቀት ማጎልበቻ ስልጠና ተስጥቷል፣

### የቅንጅታዊ አሰራር ተግባራት አፈጻጸም

ኢንስቲትዩታችን ተልዕኮውን ለማሳካት ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

#### 1.1.1. መንግስታዊ ተቋማት

- ለ70 የተመረጡ የከተማ የውሃ አገልግሎቶች ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ቅድመ-ሁኔታዎች እየተሰሩ ሲሆን ከመስኖ ልማት ኮሚሽን ጋር ለ34786 ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት የሚያስችል የአምስት ዓመት ስምምነት የተፈራረምን ሲሆን፣ በተፈራረምነው መሰረት ለ40 ባለሙያዎች ስልጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ስልጠናውን በስፋት ለመጀመር በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት "Gap servay" ለመለየት ጥናት እየተካሄደ ይገኛል፣
- ለታላቁ ቤተ-መንግስት የአንድነት ፓርክ 11 ባለሙያዎች "Switch Board and Chiller Operation and Maintenance" ላይ በተግባር የተደገፈ ስልጠና እና ለሶማሊ ክልል ውሃ ቢሮ ከ20 ወረዳዎች የውኃ አገልግሎት ተቋማት ለተውጣጡ 20 ባለሙያዎች በኦፕሬሽንና ጥገና እና ፕሮጀክት አሰተዳደር ላይ የ21 ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፣ ከADRA ኢትዮጵያ እና ከጃፓይን ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር በአራት የሙያ ደረጃዎች (በውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን፣ በመስኖና ድሬኔጅ፣ በኤሌክትሮ-ሜካኒካል እና በሶላር PV ኢንስታሌሽን እና ኦፕሬሽን ሙያዎች በአተገባበር ላይ የታዩ ክፍተቶች እና አዲሱ የቴክኒክና ሙያ ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ የሙያ ደረጃ እንዲከለስ ተደርጓል፣
- ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ እና ADRA Ethiopia ጋር በመተባበር የኢንተርፕሪነርሽፕ ክህሎት ማሰልጠኛ 2 ሞጁሎች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፣

**መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች**

- ከIRC-WASH በጋራ ሊያሰራን የሚችል ዓመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት Blended Learning System (E-learning & Face to face) የስልጠና ዘዴ በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ እንዲከለስ ተደርጎ ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ለአንድ የኢንስቲትዩቱ አመራር እና አንድ ባለሙያ የልምድ ልውውጥ እና ጉብኝት ዕድል በኔዘርላንድ ሀገር እንዲያገኙ ተደርጓል፣
- ከ "Water-Aid Ethiopia" ጋር የአምስት ዓመት የመግባቢያ ሰነድ በተፈራረምነው መሰረት ከአሮሚያና አማራ ክልል 23 ከተሞች ለተወጣጡ 129 ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 17 የስልጠና ሞጁሎች የመከለስ ሥራ የተጠናቀቀ በመሆኑ ከሌላ SCRS-WASH ጋር ስልጠና እንድንሰጥ ድርጅቱ እያመቻቸ ይገኛል፣
- ከ UNICEF ጋር በመሆን ለሶማሌ ክልል፣ ለአፋር ክልል እና ለአማራ ክልል ፕሮጀክት ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የድጋፍ ስምምነት ተጠናቆ ሥራው በሶማሌ ክልል የተጀመረ ሲሆን፣ በሌሎች ክልሎችም ለማስጀመር በሂደት ላይ ነው፣
- ከፕላን ኢንተርናሽናል-ኢትዮጵያ ጋር በመሆን በደቡብ እና ጋምቤላ ክልል ወጣቶችን ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችል implementation of Youth Economic Empowerment (YEE) የሚል ፕሮጀክትን ለመተግበር በተፈራረምነው ውል መሰረት ለስልጠና ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የስልጠና የሶላር ላቦራቶሪ ዕድሳትና ግብዓት የማሟላት ሥራ በጀት ተመድቦ እየተሰራ ይገኛል፡፡ እንዲሁም ለኢንስቲትዩቱ የሶላር ላብ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች በ19022 ዩሮ ተገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ የገባ ሲሆን፣ በሶላር ላይ በጋራ ስልጠና ለመስጠት የካሪኩለም ዝግጅት ሥራ ተከናውኗል፣

- ከ GIZ ጋር በመሆን ለዘርፉ ባለሙያዎች በsolar-powered irrigation system ላይ ስልጠና ለመስጠት ሁለት የኢንስቲትዩታችን ባለሙያዎች የአሰልጣኝነት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጎ ከጥር ወር 2014 በጀት ዓመት ጀምሮ ለ80 የዘርፉ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት ፕሮግራም ተይዟዋል፣
- ከPeople in Need ጋር ስትራቴጂክ የጋራ መግባቢያ ሰነድ በተፈራረምነው መሰረት ከይርጋ-ዓለም ከተማ ውሃ አገልግሎት አራት ባለሙያዎች በ"Pump, Geneset and Switch board operation & Maintenance" ላይ ለሃያ ቀናት ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጓል፣
- ከ "water witness international" ጋር በመሆን በውሃው ዘርፍ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ፖሊሲን ሥራ ላይ በማዋል የአገልግሎት አሰጣጥና የውሃ ሀብት አስተዳደርን በማሻሻል ዘላቂነት ያለው የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን ለሁሉም የሚለውን SDG ግብ ለማሳካት ወደ ተግባር ሊለወጡ የሚችሉ 4 ምርምሮችን ለማካሄድ የመግባቢያ ሰነድ ፊርማ በተፈረመው መሰረት የ4 ምርምር ፕሮፖዛሎች ተገምግሞና አማካሪ ቡድን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ተገብቷል፣

**የ6 ወራት የፋይናንስ አጠቃቀም**

በኢንስቲትዩቱ በመደበኛ ከተመደበው ብር 17,815,000 ውስጥ እስከ 6 ወራት መጨረሻ የተመዘገበው አፈፃፀም 16,131,634.29 ብር ነው፡፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ ሲሰላ 91% ነው፡፡ እንዲሁም ለካፒታል ፕሮጀክቶች የተያዘ አጠቃላይ ካፒታል በጀት ዕቅድ 42,220,000 ብር ሲሆን፣ የተመዘገበው አፈፃፀም 12,813,099.63 ብር ነው፡፡ አፈፃፀሙም በመቶኛ ሲሰላ 30.3% ነው፡፡

## III. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

➢ ሚኒስትር መ/ቤቱ

- የዉሃ ኮሚሽንና የተፋሰሶች በለሥልጣን  መፍረስ ጋር ተያይዞ የባንክ አካዉንት ዝዉዉር ጊዜ መዉሰድ፣ለዚህም የተወሰደዉ መፍትሂ ከሚመለከታቸዉ የተቋማቱ የሥራ ክፍሎች(ንብረት፤ኦዲት፤ፋይናንስና ሰዉ ሀብት አስተዳደር) እንዲሁም ከፋይናንስ ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት በመሥራት ችግሮቹን ለማቃለል ተሞክሯል፡፡

- ከሽ ፍሎዉ በጊዜ አለመቅረብና ከቀረበ ቦኃላም ፈጣን ምላሽ አለማግኘት ለዚህም የተወሰደዉ መፍትሄ ከፋይናንስ ሚኒስቴር ጋር በቅርባት በመገናኘት የተከለሰ ዕቅድና መረሃ ግብር ተዘጋጅቷል፤፤
- የግንባታ ግብዓት(ሲሚንቶ) ገበያ ላይ አለመገኘት ለዚህም የተወሰደዉ መፍትሄ ለተቋራጮች አስፈላጊዉን የጋራ ግንዛቤ መፍጠርና እንዲሁም ለአምራች ድርጂቶች የድጋፍ ዳብዳቤ መጻፍ
- የኢት/ያ ሽፕንግ ላይን ከፍተኛ ወጋ መጨመር(ከ1000 ዶላር ወደ 11000 ዶላር)፣
- የብድር ገንዘብ አጠቃቀም ላይ ፈጣን ምላሽ ከፓርትነሮች አለመገኘት
- በዉጪ ምንዛሪ እጥረት ምክኒያት LC በጊዜ አለመፈጸም

➢ **ከተጠሪ ተቋማት የዉሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት**

*የጋጠሙ ችግሮች*

- የስልጠና መሳሪያዎች እጥረት እና የስልጠና መሳሪዎች ጥገና ላይ የአቅም ውስንነት የሚታይበት መሆኑ፣
- በሙያ ብቃት ምዘና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በተደጋጋሚ ቢሰጥም የዘርፉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት ለማግኘት ያላቸው ፍላጎት አናሳ መሆን፣
- IFMIS አሰራርን ባለሙያው በደንብ አውቆ መስራት ላይ ችግር ያለ መሆኑና የሲስተም መቆራረጥ ሥራን እያጓተተ መሆኑ፣
- የግዢዎች ሂደት ረጅም የመሆኑና በወቅቱ ያለመፈፀሙና የ "Borehall Camera" የማሰልጠኛ መሳሪያ ያለመጠገን ሥራ ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩ፤
- አንድ የመቆፈሪያ ማሽን በብልሽት ምክንያት ለረጅም ጊዜ መቆሙ እንዲሁም በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሙያ የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት ለመስጠት የሪግ መቆፈሪያ ማሽን ሰርቪስ ለማድረግ ተፈትቶ ሳይጠገን የቆየ በመሆኑና አገልግሎት መስጠት ባለመቻሉ በቁፋሮ ቴክኖሎጂ ሙያ ለመመዘን የተመዘገቡ 26 ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት መስጠት ያለመቻል፣
- በፀጥታ ችግር ምክንያት ከአማራና አፋር ክልል በተያዘው ዕቅድ መሰረት ሰልጣኞች መምጣት ያለመቻል፣

*የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች*

- የአቅም ውስንነትን ለመፍታት ከሌሎች የትምህርትና ስልጠና እና የዘርፉ ተቋማት ጋር አብሮ ለመስራት ቅንጅት በመፍጠር እና የተለያዩ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀትከለጋሽ ድርጅቶችና መንግስታዊ ተቋማት ሀብት የማፈላለግ ሥራ ተሰርቷል፣
- የሙያ ብቃት ምዘና አገልግሎት አስፈላጊነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ በተደጋጋሚ እየተሰራ ነው፣
- የ IFMIS ስልጠና ለመስጠት በዝግጅት ላይ መሆኑና ጥገናዎች እንዲካሄዱ ጥረት እየተደረገ መሆኑ፡፡

## IV. መጠቃለያ

የሚኒስቴር መ/ቤቱና ተጠሪ ተቋማት በበጀት ዓመቱ ለስድስት ወራት እንዲሰሩ ከታቀዱት ዋና ዋና ተግባራት ከላይ በዝርዝር የተቀመጠ ስሆን ከፊዝካል ሥራዎችና በበጀት አጠቃቀም በተመለከተ ከዘርፍ ዘርፍ የተለያየ ብሆንም ጥሩ አፈጻጸም የታየበት መንፈቅ ዓመት ልባል ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ሚንስቴር መ/ቤቱም ሆኔ ተጠሪ ተቋማቱ በሚፈለገዉ ደረጃ ግዴታቸዉን መወጣት እንዲችሉ የተጀመረዉን የሪፎርም ሥራ በጊዜ ማጠናቀቅና ተጀምረዉ ሳይጠናቀቁ የቆዩት ፕሮጀከቶች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራበት ይሆናል፤፤